# ይቅር ተባባሉ

## ይቅርታ በመንፈሳዊና ሥነልቦናዊ እይታ

ከበደ በከሬ

እርማት፡- መጋቢ ስሜ ታደሰ

*የኮምፒዩተር ለቀማ፡ ወ/ሮ ዘውዲቱ በቀለ*

ራዕይ አሳታሚ
አዲስ አበባ 2000 ዓ.ም.

# ይቅር ተባባሉ

ደህንን መጽሐፍ ያስ አሳታሚው ፈቃድ ማባዛት ወይም እንደገና ማሳተም በሕግ የተከለከለ ነው።
© 2000 ዓ.ም. የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

All rights reserved.

ራዕይ አሳታሚ
የፖ. ሳ. ቁ 2332
አዲስ አበባ

RP-22 2M

## ምሥጋና

ይህን መጽሐፍ እንዲጽፍ ምሕረቱን ላበዛልኝ ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይድረሰው። ውድ ጊዜያቸውን በመሰዋት የተባበሩኝን ባለቤቴን ዘውዲቱ በቀለንና ልጆቼንም ርሆቦት፣ ናሆም፣ ኑፍታሌ እና ኬና ከበደን እግዚአብሔር ይባርካቸው። በተጨማሪም የመጽሐፉን ረቂቅ በማንበብ ገንቢ አስተያየትና እርማት ለሰጡኝ አቶ ደረጀ በቀለ፣ አቶ ብሩ ሮበሌ፣ መጋቤ ካሳሁን አብዩ፣ መጋቢ ይልማ ዋቄ፣ መጋቢ ስሜ ታደሰ፣ አቶ ሰማው መኮንን፣ ወ/ሮ መኮንን አዳሙ የእግዚአብሔር ሰላምና በረከት ይብዛላችሁ እላለሁ። እንዲሁም በምክርና በጸሎት ከጎኔ በመሆን ላበረታታችሁኝ ሁሉ ልባዊ ምስጋና አቀርባለሁ።

# 1
# ይቅርታ ምን አይደለም?

ይቅርታ በዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ ከሰዎች ጋር ግንኙነት ስናደርግ የምንሰማው ቃል ነው። አንዱ ለሌላው ስብዓዊ ትሕትናን ለመግለጽ ይጠቀምበታል። እንግዳ የሆነን ሰው አንድን ነገር ለመጠየቅ «ይቅርታ- የእኔ ወንድም ወይም እህት» ይባላል። በታክሲ ውስጥ ወንበር ላይ ለመቀመጥ ሲያልፍ ገፍተር አድርጎ ያለፈ ሰው «ይቅርታ» ይላል። በድንገት ወይም ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት በደል ያደረሰ ሰው ሁሉ «ይቅርታ» ካለ በኋላ የተበደለው ሰው ከዚህ አልፎ እርምጃ መውሰድ ይከብደዋል። ከዕለት ተዕለት አጠቃቀማችን ይቅርታ የሚለው ቃል ያለፈውን ታሪክ የሚዘጋና አዲስን ግንኙነት የሚያመለክት ነው።

ይቅርታ በልጆችና በአዋቂዎች ዘንድ የተለመደ ነው። ቃሉ ለአንደበታችን አዲስ ባይሆንም ምስጢሩ ግን ለሁሉም በተመሳሳይ ደረጃ የተገለጠ ስለመሆኑ እርግጠኛ መሆን አይቻልም። ስለዚህ ይቅርታን በስፋት ከመመልከታችን በፊት ትርጉሙን በሚገባ ማጤን አስፈላጊ ነው። ይቅርታን በሁለት መልክ መመልከት ይቻላል። የመጀመሪያው ይቅርታ ያልሆነውን በመግለጽ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ይቅርታ የሆነውን ትክክለኛ ነገር በማብራራት ነው። በሁለቱም እይታ ይቅርታን በስፋት መገንዘብ ይቻላል። ስቅድሚያ ይቅርታ ያልሆነውን ነገር እንመለከታለን።

*ከዕለታት አንድ ቀን በአንዲት አጥቢያ ቤተክርስቲያን እግዚአብሔርን ለማምለክ ሄድኩኝ። ሰዎች ሞልተው በለነበር በስተመጨረሻ ባለው አግዳሚ ወንበር ላይ አንዱን ጠጋ በልልኝ ብዬ ተቀመጥኩ። መዘምራን መዝሙራቸውን እንደ ጨረሱ አንድ ወደ ሃምሳ ዓመት የሚጠጋ ጎልማሳ ለመስበክ ምስባኩ ላይ ወጣ። የስብከቱ መልዕክት የተመሠረተው በኤፌሶን መልዕክት ውስጥ «እርስ በርሳችሁ ይቅር ተባባሉ» በሚለው ቃል ላይ ነበር። የስብከቱም ርዕስ ይኼው ነበር። ሰባኪው ስለ ይቅርታ ሲሰብክ የሚከተሉትን ዋና ዋና አሳቦች ለመያዝ ሞክሬ ነበር። «የሌሎች ሰዎችን በደል አለመቁጠር ነው»፣ «ሰዎች በድለውን ይቅርታ ከጠየቁን ይቅር ብለናቸው ከእነርሱ ጋር የነበረንን ግንኙነት ማደስ አለብን»፣ «ክርስቶስ ኃጢአተኞችን እንደሚታገስ እኛም እንዲሁ የሚበድሉንን ሰዎች መታገስ ያስፈልገናል»፣ «ለበደሉን ሰዎች ይቅርታ አድርገናል እያልን ነገር ግን ከእነርሱ ጋር እርቅ ሳንፈጥር መኖር ትክክል አይደለም» እና «የበደሉንን ሰዎች ይቅር ካልን በኋላ በምንም ተዓምር እነርሱ በእኛ ላይ ያደረሱትን በደል ማሰብና ማስታወስ የለብንም። በደል መረሳት አለበት» የሚሉ ይገኙ -በታል።*

ሰባኪው በዚህ ርዕስ ላይ ሲናገሩ ከጎኔ የነበሩ ሰዎች ከንፈራቸውን እየመጠጡ ይሰሙት ነበር። ምናልባት የበደላቸው ወይም የበደሉት ሰው ስለሚኖር መልዕክቱ በሆነ መንገድ ልባቸውን ነክቶ ይሆናል ብዬ አሰብኩ።



ከዚህም በተጨማሪ በእርግጥ እነዚህ የተጠቀሱ አሳቦች ይቅርታን በትክክል መግለጥ የሚችሉ ትክክለኛ ነጥቦች ነበሩ ወይ? የሚል ጥያቄም ተጭሮብኛል። እነዚህ ሰባኪው የዘረዘራቸው ነጥቦችን ስትመለከቱ ሰባኪው ስለይቅርታ ያስተላለፈው መልዕክት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው ይመስላችኋልን?

ከይቅርታ ጋር የሚመሳሰሉ ነገር ግን ይቅርታ ያልሆኑ ብዙ አሳቦችና ድርጊቶች አሉ። እነዚህ ነገሮች ከይቅርታ ጋር የሚያመሳስላቸው አንዳንድ ሁኔታዎች ቢኖሩም ለብቻቸው ይቅርታን መግለጽ አይችሉም። እነዚህን አሳቦች ለይቶ ማወቅ ስለ ይቅርታ ትክክለኛ ግንዛቤ ኖሮን በሕይወታችን ተግባራዊ እንድናደርግ ያግዘናል።

ይቅርታ፡- የተፈጸመው በደል አግባብነት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ አይደለም

ተበዳይ ለበዳይ ይቅርታ በሚያደርግበት ወቅት የተለያዩ ምክንያቶችን ፈልጎ የበዳይን ድርጊት ማጽደቅ አይደለም። ሰዎች በምንም ሁኔታ ውስጥ ሆነው ለሚፈጽሙት ክፉ ድርጊት ተጠያቂዎች ናቸው። አንዳንድ ጊዜ በዳዮች ሁኔታዎች ከአቅማቸው በላይ ሆነው ወይም በሰይጣን ተገፋፍተው በደል እንደፈፀሙ ሲናገሩ ይችላሉ። በእርግጥ ምክንያታቸው ትክክል ሊሆን ይችላል። ሆኖም ለፈጸሙት በደል በቂ ምክንያቶችን በመዘርዘር ብቻ ለበደሉ ተጠያቂ ከመሆን ማምለጥ አይችሉም። ለሰዎች ይቅርታ ስናደርግላቸው «የፈጸማችሁት በደል ትክክል ነው ወይም በደሉን እንድትፈጽሙ ያደረጋችሁ በቂ ምክንያት ስላላችሁ በመሆኑ ከተጠያቂነት ነጻ ናችሁ» ማለታችን አይደለም።

የደቡብ አፍሪካ የሰላምና እርቅ ኮሚሽን ሰብሳቢና የአንግሊካን ቤተክርስቲያን ጳጳስ የነበሩ ደስሞን ቱቱ «ይቅርታ ማድረግ ማለት የተከሰተውን ነገር ምንም እንዳልሆነ አሳንሶ መገመት ሳይሆን የሆነው ነገር አሳሳቢ ጉዳይ መሆኑን መቀበልና ከሆነው ደረጃ በምንም መልኩ አለማሳነስ ነው። ነገር ግን በአእምሮአችን ውስጥ የተቀመጠው ቁስልና ትዝታ የመኖር ሕልውናችንን እንዳይመርዝ ማስወገድ ነው»[1] በማለት ተናግረዋል። በዚህ አገላለጽ ውስጥ ስለይቅርታ ቢያንስ አራት ዋና ዋና አሳቦችን ማውጣት ይቻላል። እነርሱም፡-

- ለበዳይ ይቅርታ ማድረግ በዳይ የፈጸመው በደል እያለ ምንም ነገር እንዳልፈጸመ መግለጽ አይደለም። ይቅርታ በደል እንዳልተፈጸመ አያስብም ወይም የሆነውን በደል አይክድም። በአዎንታዊ መልክ ሲገለጽ ሰዎችን/በዳዮችን/ ይቅር ማለት ይቅርታ በደል መኖሩን በመቀበል ይጀምራል። አንድ ሰው ሌላው እንደ በደለው ካላሰበ ወይም ካልተቀበለ ስለምን ጉዳይ ይቅር ማለት ይችላል? ይቅርታ የሚኖረው ተበድያለሁ የሚል ወገን ሲኖር ነው።

---

[1] Tutu, D. p. 271

የመዝራትና የማጨድ መንፈሳዊ ሕግስ በዚህ ሁኔታ ውስጥ እንዴት ተግባራዊ መሆን ይችላል? «ሰው የሚዘራውን ያንኑ ያጭዳል። ሥጋዊ ምኞቱን ለማርካት የሚዘራ፣ ከሥጋ ጥፋትን ያጭዳል፣ መንፈስን ለማስደሰት የሚዘራ ግን ከመንፈስ የዘላለምን ሕይወት ያጭዳል» (አ.መ.ት.) (ገላ6:7-8)። ሰዎች የዘሩትን እንዲያጭዱ ማድረግ መንፈሳዊ ሕግ በመሆኑ እኛን በተከታታይ የሚበድሉትን ሰዎች ይቅር ማለት የመዝራትና የማጨድ ሕግ ተግባራዊ እንዳይሆን ጣልቃ መግባታችን አይሆንም ወይ? አንድ ሰው እሁንም እሁንም ተመሳሳይ ዓይነት በደል በእኛ ላይ ከፈጸመ በኋላ ወደ እኛ መጥቶ ሁልጊዜ ይቅርታ የሚያገኝ ከሆነ ያ ሰው ኃጢአት በመሥራት እንዲቀጥል አስተዋጽኦ ማድረጋችን አይደለም ወይ?

አንድ ሰው በሚናገራቸው ቃላትና በሚያደርጋቸው ድርጊቶቹ በተደጋጋሚ በደልን የሚፈጽም ከሆነ ለዚያ ሰው ይቅርታ ማድረግ ይከብዳል። በሰዎች ተበድሎ ይቅርታ ለማድረግ የማይከብደው ሰው ቢሆንም እንኳ አንድ ሰው በተደጋጋሚ ሲበድል ይቅር ለማለት የሚኖረው የልብ መነሳሳት ይቀንሳል። በተበዳይ አእምሮ ውስጥ ብዙ ዓይነት አሳቦች መመላለስ ይጀምራሉ። «ይህ ሰው እንዴት ቢያበበኝ ነው?» «መንፈሳዊ ሰው መሆን ሰላማዊ ያደርጋል እንጂ የሰው መጫወቻ ያደርጋል ወይ?» እያለ ይቅርታ ከማድረግ ይልቅ ለመበቀል ይነሳሳል። ሪክ ዋረን «አንድ ሰው በተደጋጋሚ ሲበድልህ በደሎቹን ወዲያውኑ ይቅር እንድትል በእግዚአብሔር ብትታዘዝም፣ መበደሉን እንዲቀጥል እንድትፈቅድለት ግን አይጠበቅብህም» ብለው ተናግረዋል።[2]

በዚህ አሳብ መሠረት አንድ ሰው ከተበደለ ይቅርታ ማድረግ እንደሚገባው መለኮታዊ ትዕዛዝ ተሰጥቶታል። ነገር ግን ይህ በደል ከአንድ ሰው ተከታታይነት ባለው ሁኔታ እንዳይደርስበት ማድረግ መብቱ ነው። ያለማቋረጥ መበደል የእግዚአብሔር አሳብ አይደለም። ስለዚህ ከዚህ ዓይነት ግንኙነት ውስጥ መውጣት እንደሚቻል ያሳስባል። በዳይን ይቅር ማለት ከእርሱ ወይም ከእርስዋ ጋር ወደፊት ኅብረት መቀጠልን ላያመለክት ይችላል። የወደፊት ግንኙነት የሚወሰነው በዳይ በቀጣይነት በደል መፈጸሙን ሲያቆም ነው። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ሰብዓዊ ግንኙነት በሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ መሆኑን እንገነዘባለን። ለመልካም ግንኙነት የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች በማይሟሉበት ጊዜ ተገቢውን ወሰን በማበጀት የራስን መብት የማስከበር እርምጃ መውሰድ ተገቢ መሆኑን መቀበል የግድ ይሆናል።

ከመዝራትና ማጨድ ሕግ አንጻር ከላይ የተጠቀሱት አሳቦች ጌታ ኢየሱስ ካስተማረው ትምህርት ጋር እንዴት አብሮ ሲሄዱ ይችላሉ? በእርሱ ትምህርት ውስጥ ይቅርታ ገደብ የተቀመጠለት እርምጃ አይመስልም። ጌታ ኢየሱስ ለተጸጸተ በዳይ ይቅርታ ማድረግ ወሰን የሌለው ጉዳይ መሆኑን ማስተማሩ የሰዎችን ተፈጥሮአዊ ሁኔታ አስመረዳቱ ነው ወይስ መልዕክቱ ምንድነው? በእርግጥ ንስሐ ለሚገባ ሰው ይቅርታ በማንኛውም ሁኔታ

[2] ሪክ ዋረን፡ ዓላማ መር ሕይወት. ገጽ 152



ውስጥ መስጠቱ የወንጌል ትምህርት ነው። ይህ እውነት ግን እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆን መመልከት ተገቢ ነው። በሰብዓዊ ግንኙነት ውስጥ በደል በሚፈጸምበት ጊዜ ተበዳይ ወደ በዳይ በመሄድ ወንድሙ በእርሱ ላይ ያደረሰውን ሁኔታ በግልጽ መንገርና በጉዳዩ ላይ መነጋገር የመጀመሪያ እርምጃ ነው። «ወንድምህ ቢበድልህ ገሥጸው» ይላል።

ስለዚህ እንዱ ሌላውን ለመገሰጽ ዕድል አለው። ተበዳይ ለበዳይ አሳቡንና ስሜቱን ይገልጽለታል። በዚህ ውይይት ጊዜ በዳይ በእርግጥ ያደረሰው በደል ሳይኖር ተበደልኩ የሚለው ወገን በስህተት እንዲህ ያለበ ከሆነ ራሱ ንስሐ ይገባና በዳይ የተባለውን ይቅርታ ይጠይቃል። በእርግጥ ደግሞ በዳይ ወንድሙን በድሎ ከሆነ ይቅርታ ሊጠይቅ ይገባል። በዚህ ሁኔታ በዳይ በተደጋጋሚ ሌላውን መበደሉን ተረድቶና ተጸጽቶ ይቅርታ ቢጠይቅ ይቅርታን መስጠት ያስፈልጋል። ይህ ሁለተኛው እርምጃ ነው። በዳይ በተበዳይ ላይ ባደረሰው በደል መጸጸትና ይቅርታንም ፈልጎ ወደ ተበዳይ መምጣት እንደሚችል ሁሉ ተበዳይም ወደ በዳይ መሄድ ይችላል። ከላይ በተጠቀሰው አሳብ ውስጥ ተበዳይ ወደ በዳይ እንደሚሄድና እንደሚገሰጽ ተመልክቷል። እነዚህ ሁለቱ እርምጃዎች በሚኖሩበት ጊዜ ተከታታይነት ባለው ሁኔታ ለበዳይ ይቅርታ ማድረግ መንፈሳዊነት እንጂ ጅልነት አይደለም።

በዳይ በፈጸመው በደል ተጸጽቶ ይቅርታ ባይጠይቀስ? በዳይ ተጸጽቶ ይቅርታ ካልጠየቀ በስተቀር ለእርሱ ይቅርታ አይደረግም ማለት ባይቻልም በቀጣይነት ግንኙነት ማድረግ ግን ተግዳሮት አለው። ተጸጽቶ ከመጣ ሰው ጋር በመነጋገር ችግሩን መሰወጥ የሚቻልበት ሁኔታ ይኖራል። ወደ እኛ በመቅረቡም ከእርሱ ጋር ግንኙነት ለማድረግ ነፃነት ይሰማናል። በዳይ በፈጸመው በደል ምንም ጸጸት የማይሰማው ከሆነ ይቅር ማለት እንችላለን። ነገር ግን ከእርሱ ጋር ወደፊት ግንኙነት ለመመሥረት የሚያስችል መቅረብ ላይኖረን ይችላል። በዳይ ባለመጸጸቱና ወደ በዳይ መጥቶ ይቅርታ ባለመጠየቁ ምክንያት በእርሱ ላይ ቂም መያዝና ለመበቀል ማሰብ የራስን ሕይወት ከመጉዳትም ባሻገር የሁለቱንም ግንኙነት አሁን ካለው በላይ ሊያበላሽ ይችላል። ይህ ሰው አንድ ቀን ሕሊናው ወቅሶት ንስሐ ቢገባም እርሱን እንደገና ለመቀበል ልባችን ክፍት፣ እጃችን የተዘረጋና ፊታችን በፈገግታ የተሞላ ሊሆን ይገባል።

ፍቅር በዳይን ይቅር ለማለት ያግዛል። ይህ ማለት ግን በዳይ የሚፈጽመውን በደል በተከታታይ በእኛ ላይ እንዲፈጽም መፍቀድ ማለት አይደለም። እግዚአብሔርም ሰዎችን ይቅር የሚለው ሰዎች ለፈጸሙት ኃጢአት ተጠያቂዎች መሆናቸውን ሲረዱ ነው። ይቅርታው ሁልጊዜ የሚገኝ ቢሆንም ይህን በነጻ የሚሰጠውን ምሕረት የራሱ ማድረግ የሚችለው ግን «እኔ ለዚህ በደል ተጠያቂ ነኝ» የሚል ሰው ነው። እኛም ለበዳዮች ይቅርታ ለማድረግ የሚፈቅድ ልብ ሊኖረን ያስፈልጋል። ፍቅር ለተፈጸመው በደል ይቅርታ ሲያደርግ በዳይ ወደፊት ተመሳሳይ ዓይነት በደል እንዳይፈጽምም ወሰንን በማበጀት ይገለጻል። ፍቅር አንድ ጊዜ የበደለን ሰው ሁልጊዜ እንዲበድለን አይፈቅድም። በዳይ ተጠያቂነት እንዲሰማው

አለማድረግ በዳይን መውደድ ሳይሆን ኃጢአት እየፈጸመ ፍርድን በራሱ ላይ እንዲያከማች ማድረግ ነው። ይህ ደግሞ የፍቅር ተግባር አይደለም። ፍቅር በደልን ይሸፍናል ነገር ግን በዚህ ሽፋን ሰዎች ኃጢአት መሥራታቸውን እንዲቀጥሉበት አያደርግም። ኃጢአትን መተው ወደሚችሉበት የሕይወት ደረጃ እንዲመጡ ያግዛቸዋል። ይህ ከሚፈጸምባቸው መንገዶች አንዱ ለሥዎች ለሚሠሩት ነገር ኃላፊነት እንዲወስዱና ተጠያቂነትን በማስተማር ነው።

አንዳንድ ጊዜ በሰዎች መካከል የሚታየው ሁለቱም ወገኖች (በዳይና ተበዳይ) ማድረግ የሚገባቸውን አዎንታዊ ነገር ሳያደርጉ እንዲሁ መተያየት ነው። በዳይ ስለፈጸመው በደል ንስሐ መግባት አይፈልግም። ተበዳይም በዚህ ጉዳይ ላይ ለበዳይ ይቅርታ ለማድረግ አይፈልግም። በዳይና ተበዳይ ተዘጋግተው ይኖራሉ። አንዳንድ ጊዜ በአካል ተራርቀው ሲኖሩ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ «አብሮ» እየኖሩ በውስጣቸው ግን ተለያይተው ይመላለሳሉ። በዚህ ዓይነት ሁኔታ በእያንዳንዳቸው ልብ ውበጥ አንዱ በሌላው ላይ ያለው ጥላቻ እያደገ ይሄዳል። ይህ የእርበ በርስ ጥላቻ ደግሞ ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላ ትውልድ ሲተላለፍ ይችላል። እውነተኛ ንበሐና ይቅርታ በቀላሉ ሲፈውሰው የሚችል በደል ከትውልድ ወደ ትውልድ ለመሸገር ዕድል ያገኛል።

በአገልግሎት ውስጥ በተለይ ደግሞ በማማከር አገልግሎት እንዳስተዋልኩት ከሆነ አንዱ ሌላውን ወገን በተከታታይ በሚበድልበት ጊዜ ዝም ብሎ መቻል አዎንታዊና አሉታዊ ውጤት ይኖረዋል። በአንዳንድ ሁኔታዎች ተበዳይ በዳይ ያለማቋረጥ በድል ሲፈጽምበት በሁኔታው ከመገረሙ የተነሣ ንስሐ ገብቶ ከከፉ ንግግር ወይም ድርጊት ሲመለስና ለተበዳይም ትዕግሥት ብዛት ምስጋናና አክብሮትን ሲሰጥ ይስተዋላል። በተቃራኒው ደግሞ ተበዳይ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ሲበደል ዝም ብሎ በዳይን መሸከሙ እንደ ሞኝነት ተቆጥሮ የባሰ በደል የሚደርስበትና እንዲያውም በዳይ ተበዳይን እንደ ሰው ባለመቁጠር ከእርሱ ወይም ከእርስዋ ጋር የሚኖረውን ግንኙነት የሚያቋርጥበት ሁኔታ ያጋጥማል።

ስለዚህ በስብዓዊ ግንኙነት ውስጥ ተከታታይነት ባለው ሁኔታ የሚመጣውን በደል መታገስ ግልጽ የሆነ ዓላማ ካለው (ለምሳሌ በዳይ ወደ አእምሮው ተመልሶ ራሱን መመልከት እንዲችልና ንስሐ እንዲገባ ለመርዳት) ቃሉን ማዕከል ባደረገ ሁኔታ መሸከም መልካም ነው። ነገር ግን ያለማቋርጥ የሚደርሰውን በደል ዝም ብሎ መሸከም አሳስፈላጊ ዋጋ መክፈል ይሆናል። በዚህ ሂደት ውስጥ የሚያልፍ ሰው ከእግዚአብሔር ዘንድ ምሪትንና ጥበብን መጠየቅ በዓውዱ ውስጥ ምን ዓይነት እርምጃ መውሰድ እንደሚገባው ለማወቅ ያግዛል።

*ገበየሁና መሰለች (እውነተኛ ስማቸው አይደለም) ባልና ሚስት ሲሆኑ ትዳር ከመሠረቱ ዘጠኝ ዓመት አልፎአቸዋል። ልጆችንም ወልደዋል። ገበየሁ ከቃል ኪዳን ሚስቱ ውጭ የሴት ጓደኛ እንዳለው በሠፈር ይወራል። ወ/ሮ መሰለች ግን ይህን ስትሰማ «የባለቤቴን ስም ለማጥፋትና በትዳሬ ቀንተው ነው እንጂ እርሱ እንዲህ ዓይነት መጥፎ ነገር አያደርግም» በማለት እጥብቃ ትቃወማለች። ባሉዋ በእርስዋ ብቻ ታማኝ ሆኖ*



*እንደሚኖር ታምናለች። ከዕለታት አንድ ቀን ጎረቤትዋ የሆነች ሴት ባልዋ ይህን ነገር ወደሚያደርግበት ሥፍራ ወስደቻትና ወ/ሮ መሰለች ሁኔታውን በዓይንዋ አየች። ባልዋ ማታ ወደ ቤት ሲገባ ሁኔታውን ጠየቀችው። አቶ ገበየሁም ነገሩ እውነት መሆኑን በማመን ይቅርታ ጠየቃት። ወ/ሮ መሰለች ባልዋ ዳግመኛ ይመለሰበታል ብላ ባታስበውም እርሱ ግን ከስመደው ባሕርይው አልተለየም። አንድ ቀን ደግሞ ሴት ጓደኛውን ይዞ በገዛ ቤቱ ውስጥ አያሉ ወ/ሮ መሰለች ከሄደችበት ሥፍራ ከተፍ አለች። ያየችውን ነገር ማመን አቃታት። አሁንም ይቅርታ ይጠይቃትና ከእርስዋ ጋር መኖር ይጀምራል። በዚሁ ሁኔታ አብረው አያሉ የፍች ጥያቄን አቅርቦ ከወ/ሮ መሰለች ተፋቶ አዲለዋን ሴት ጓደኛውን አገባ።*

ከዚህ ታሪክ ከመጠን ያለፈ ትዕግስትና መቻል በሁለት ወገኖች መካከል ያለውን ግንኙነት ከማጠናከር ይልቅ እንዴት ከፉኛ ሲጎዳ በሚችል መልኩ ኅብረቱን ሊያፈርስ እንደሚችል እንመለከታለን። ስለዚህ በዳይን መሸከም ሲያመጣ የሚችለውን አዎንታዊና አሉታዊ ውጤቶችን ከወዲሁ መገመት ሲመጣ ካለው ያልተጠበቀ ውጤት ያድናል ወይም ዝግጅት ለማድረግ ያግዛል።

## ይቅርታ ከእርቅ የተለየ ነው

በስብዓዊ ግንኙነት ውስጥ በደል ሲደርስብን ለበዳይ ይቅርታ ማድረግ መሠረታዊ መርሕ ሲሆን መታረቅ ግን ሁልጊዜ ሳይሳካ ይችላል። ይቅርታ በእግዚአብሔር ጸጋ ድጋፍ በልባችን የሚከናወን ሂደት ሲሆን የበዳይ አዎንታዊ ድርሻ ምንም ሳያስፈልገን ለበዳይ ይቅርታ ማድረግ እንችላለን። ይቅርታ ይቅርታ ለማድረግ የአንድ ወገን ፈቃደኝነት ብቻ በቂ ይሆናል። ይቅርታ በአብዛኛው በአንድ ሰው አእምሮ ውስጥ ሲፈጸም የሚችል ክስተት ነው። እርቅ እንዲመጣ ግን ሁለቱም ወገኖች ፈቃደኞች መሆን አለባቸው። ይቅርታ ለእርቅ መንገድ የሚጠርግ ሂደት ቢሆንም ሁልጊዜ ወደ እርቅ ላያመራ ይችላል። እርቅ የሚመጣው በዳይና ተበዳይ ወገኖች ድርሻቸውን ሲወጡና ለፈጸሙት በደል ኃላፊነት ወስደው ተገቢውን እርምጃ ሲጀምሩ ነው።

በእብዛኛው ሰዎች ይቅርታ ማድረግን ለማሰብ በዳዩ ቢያንስ ይቅርታ መጠየቅ አለበት ብለው ያስባሉ። የእኛ ይቅርታ ማድረግ በዳዩ ለሳደረሰው በደል እንዲጸጸት ሳያደርገው ይችላል። በዳይ በፈጸመው በደል ባይጸጸትም ወይም ድርጊቱን ባይለውጥም ይቅር ማለት እንችላለን። የእኛ ይቅርታ የሌላውን ሰው ድርጊት ወይም ባሕርይ ሳይለውጥ እንደሚችል መረዳት ትኩረት መደረግ ያለበት በግል ባሕርይና ድርጊት እንጂ በሌሎች ሰዎች ድርጊትና ባሕርይ ላይ እንዳይሆን ያደርጋል። እኛ መቆጣጠር የምንችለው የራሳችንን ብቻ ስለሆነ ራሳችንን ለመለወጥ ጥረት እናድርግ።

ይቅርታና እርቅ በተመሳሳይ ደረጃ መከናወን የሚችሉት ተበዳይና በዳይ በተፈጸመው በደል እያንዳንዳቸው እውነተኛ ንስሐ ገብተው፣ ይህም በሁለቱ

እውቅና አግኝቶ በመካከላቸው ያለው ግንኙነት እንደገና እንዲታደስ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ፍላጎትና መለጠት ሊኖራቸው ነው። በዳይና ተበዳይ የጋራ የሆነ ግንዛቤ ሊኖራቸውና ገንቢ እርምጃ ሲወስዱ እርቅ ይቅርታን ተከትሎ ይመጣል። ዴቪድ እውግስበርገር የተባለው ጸሐፊ «ንስሐ ይቅርታ ለማድረግ እንደ ቅድመ ሁኔታ የሚቀመጥ ነጥብ አይደለም፤ይህም ብቻ ሳይሆን ንስሐ ከይቅርታ በኋላ የሚጠበቅም ፍሬ አይደለም። ንስሐ ይቅርታ እንዲመጣ መንገድ የሚጠርግ ሂደት ነው»[3] ብለዋል።

በዚህ እሳብ መሠረት ለበዳይ ይቅርታ ለማድረግ የበዳይን እውነተኛ ንስሐ መግባት እንደ ቅድመ ሁኔታ መቀመጥ የለበትም። በዳይ በለፈጸመው በደል ቢጸጸትም ባይጸጸትም ይቅር ማለት እንደሚያስፈልግ ሁሉ ከይቅርታም በኋላ በዳይ እውነተኛ ንስሐ ሊገባ እንደሚችል መጠበቅም እያስፈልግም። ይቅርታ ሊታሰብ ንስሐ እንደ ቅድመ ሁኔታ እንዲሁም እንደ ውጤትም ሊቀመጥ አይገባም። እውነተኛ ንስሐ በሚኖርበት ሁኔታ እርቅን የሚያስከትል ይቅርታ ሊመጣ ይችላል። በሁለቱም ወገን የሚደረግ ንስሐና ይቅርታ ደግሞ ወደ እርቅ ይመራል። በእርቅ ደግሞ የተበላሸው ግንኙነት ይታደሳል። ስለዚህ በዳይን ይቅር ለማለት ሊቀመጥ የሚገባ መመዘኛ እንዲሁም ይገኛል ተብሎ የሚጠበቅ ፍሬ መኖር የለበትም። በሌላ አገላለጽ ይቅርታ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲሁም ምንም ፍሬ ሳይጠበቅ የሚወሰድ እርምጃ ነው።

«እርቅ ከይቅርታ ጋር ተመሳሳይ አይደለም። በሕይወትህ ላይ በደል በመፈጸም የጎዳህን ሰው እንደገና ወደ ሕይወትህ ውስጥ እንዲገባ መፍቀድና ከበደሉ የተነሳ የተሰማህን ሕመም ማስወገድ አንድ አይደሉም።»[4] በዚህ እሳብ መሠረት ይቅርታ አንድ ሰው በድሉን በሕይወታችን ላይ ያደረሰውን ጉዳት ለማከም የምንጠቀምበት መሣሪያ ነው። ይህን እለማድረግ ከበደሉ የተነሳ በእኛ ላይ የደረሰው ቁስል ሕመሙ ሁልጊዜ እየተሰማን እንዲኖር መፍቀድ ነው። እርቅ ደግሞ የበደልን እሉታዊ ውጤት ከሕይወታችን ከማስወገድ እልፎ በደሉን በማድረስ ሕይወታችንን ያቆሰለውን ሰው እንደገና ወደ ሕይወታችን ውስጥ እንዲገባ መጋበዝ ነው።

እዚህ ላይ የሁለቱን ልዩነት ከመገንዘብ ባሻገርም ማስተዋል ያለብን መሠረታዊ ነጥቦች እሉ። በዳይን ወደ ሕይወታችን እንደገና ከማስገባታችን በፊት እርሱ በፈጸመው በደል ምክንያት የተጎዳው ሕይወታችን ፈውስ ሊያገኝ ያስፈልጋል። እንዲህ ሳይሆን እንደገና ግንኙነቱን መጀመር በተበዳይ ሕይወት ላይ የሚያመጣው እሉታዊ ውጤት ያመዝናል። ከዚህም በተጨማሪ ሁለቱም የተለያዩ በመሆናቸው ተበድለን ይቅርታ በማድረግ በሕይወታችን ላይ የደረሰውን ቁስል በመፈወስ ብቻ ሂደቱን ልናቆም እንችላለን። በሕይወታችን ፈውስን ካገኘንና ከፈቀድን ደግሞ በዳይን እንደገና

[3] Augsburger, D.W. (1992). *Conflict Mediation Across Cultures*. Westminster/John Knox Press. P. 284

[4] Simon, S.B. and Simon, S. (1991) p. 206



ወደ ሕይወታችን በመጋበዝ ከእርሱ ጋር ጤናማ የሆነ ኅብረትን መፍጠር ይቻላል።

ቮልፍ የተባለው የሥነመለኮት ጸሐፊ ይቅርታ በማግለልና በማቀፍ መካከል ያለ ክስተት እንደሆነ ይናገራል። በእርሱ እይታ ይቅርታ አንዱን ወገን በማግለል የተከሰተውን ለቆቃ ይፈውሳል፤ በበዳይና ተበዳይ መካከል የተቀመጠውን የጥልን ግድግዳ ያፈርሳል። ሆኖም ግን በእነዚህ ወገኖች መካከል ያለውን ርቀት በማጥበብ ወደ አንድነት ከማምጣት ወደ መሐከላዊ ሥፍራ ያመጣቸዋል። ከዚህ ሥፍራ በሰላም መለያየትና በራሳቸው መንገድ መሄድ ወይም አንዱ ሌላውን በመቀበል ቀድሞ የፈረሰውን ኅብረታቸውን በማደስ አብረው መኖር እንዲጀምሩ ያደርጋል። የክርስቶስ ዓላማ ግን በሰዎች መካከል ምንም ዓይነት በደል ቢፈጸም ይቅር በመባባል በመታረቅ አብሮ መኖር መቻል ነው። እውነተኛ ሰላም የሚመጣው ጠላቶች በመለያየታቸው ሳይሆን ቀድሞ ጠላቶች በነበሩ ወገኖች መካከል ኅብረት ሲፈጠር ነው።[5]

እንደ ቮልፍ አመለካከት ይቅርታ በበደል ምክንያት የራቀውን ሰው ማቅረብና ሊያንስ በሁለቱ መካከል ያለውን ጥላቻ ማስወገድ ነው። በበዳይና ተበዳይ መካከል ያለው መራራቅ በይቅርታ አማካኝነት ሲጠብ በደል በእያንዳንዳቸው ላይ ያደረሰው ውስጣዊ ስብራት የፈውስ እርምጃውን ይጀምራል። በሁሉም መካከል ያለው የጠላትነት ስሜት ይወገዳል። አንዱ ሌላው በማይጠላበት እንዲሁም በማይወድበት ቀዝቃዛ ስሜት ውስጥ ይሆናል። አንዳንድ ጊዜ ይቅርታ በዚህ ላይ ሊያበቃ ይችላል። ሁለቱም ወገኖች ሕይወታቸውን በየግላቸው መኖርን ይቀጥላሉ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የቀድሞ ግንኙነታቸውን ለማደስ ጥረት ወደማድረግ ያድግና በሁለቱ መካከል እርቅ እንዲፈጠር ያደርጋል። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ይቅርታ ወደ እርቅ በማምራት ጉዞውን ይጨርሳል። ይህ የሚመረጥ ቢሆንም ይቅርታ ጠላትነትን በማስወገድ ግንኙነትን ሳያሳድስ ቢቀርም እንደ አዎንታዊ እርምጃ ሊወሰድ ይችላል።

እንግዲህ ሁለቱም የተለያዩ ነገሮች ቢሆኑም አንደኛ ይቅርታ ለእርቅ ሁኔታዎችን የሚያመቻች ድርጊት እንደሆነ ተመልክተናል። ሁለተኛው ደግሞ ይቅርታና እርቅ የጋራ የሆነ መሠረት እላቸው። ሁለቱም ተግባራዊ ለመሆን እጅግ ፈታኝና አስቸጋሪ ሂደት ውስጥ ያልፋሉ። በዚህ ሂደት ውስጥ በዳይና ተበዳይ ለግንኙነታቸው ፈውስን ለማምጣት መጨከን፣ መስጠትና ወደፊት ለመራመድ በግንዛቤ ላይ የተመሠረተ እርምጃዎችን መውሰድ ያስፈልጋቸዋል።

እርቅ ማድረግ በውስጡ ማሕበራዊ ክስተት እንዲሁም በግለሰብና በሰዎች መካከል የሚፈጸም ድርጊት እና በግለሰቡ ውስጥ የሚታየውን ሥነልቦናዊ ገጽታ ይይዛል። በድርጊት የሚገለጸው የእርቅ ገጽታ ከበዳይ ጋር ግንኙነት መመሥረትን ያጠቃልላል። የሥነልቦናዊ ገጽታው ደግሞ

[5] Volf, pp125-126

ከበዳይ ጋር የቀረበ፣ መስጠትና ታማኝነት የሚኖርበት ግንኙነትን መመሥረት መፈለግ ይሆናል። ከዚህ አንጻር ሲታይ ይቅርታና እርቅ ልዩነት ቢኖራቸውም አንዱ ሌላውን የሚደግፍና ለግንኙነት መታደስ ሁለቱም የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንደሆነ መገመት ይቻላል።

ይቅርታ የተፈጸመውን በደል መርሳት አይደለም

ለበዳይ ይቅርታ ማድረግ በዳይ ያደረሰውን በደልና በዚያም የደረሰውን ውጤት መርሳት ነውን? አንድ ሰው ለበዳይ ይቅርታ ማድረግ ቢችልም ሁኔታውን ግን ዕድሜውን ሁሉ ሊያስታውሰው አይችልምን? አንዳንዶች በሕይወታቸው ላይ የተፈጸመውን በደል እስመርሳት ያንን ክፉ ድርጊት መልሶ ላለመፈጸም ሊረዳ ይችላል ብለው ማሰባቸው ምን ያህል እውነትነት አለው?

በስብዓዊ ግንኙነት ውስጥ በደል ከተፈጸመ በኋላ ይቅርታ ቢፈጸም በደሉ ይረሳል ወይም አይረሳም ለሚለው ጥያቄ መልስ ለማግኘት እግዚአብሔር ሰዎችን ይቅር ሊል በደላቸውን ይረሳል ማለት ነውን? ይህ መርሳትስ ምን ማለት ነው? የሚሉትን ጥያቄዎችን መመለስ ለግንዛቤ ይረዳል። ሰዎች እውነተኛ ንስሐ ገብተው ኃጢአታቸውን ለእግዚአብሔር በመናዘዝ ለከፉ አሳባቸውና ድርጊታቸው ቢርቁ ከእርሱ ዘንድ ይቅርታን እንደሚያገኙ እናምናለን። እግዚአብሔር ይቅር ካላቸው በኋላ ኃጢአታቸውን ያስታውሳልን? ለሚለው ጥያቄ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ የሚል መልስ አለው:- «ዓመፃቸውን እምራቸዋለሁና፣ ኃጢአታቸውንም ደግሜ አላስብም» (ዕብ8:12)።

እግዚአብሔር አንድ ጊዜ የሰዎችን ኃጢአት ይቅር ካለ በኋላ በእርሱ ላይ የተፈጸመውን በደል ዘወትር አያስበውም፣ አያሰላስለውም፣ አያወራውም። ይህን የማያደርገው ስለማያስታውሰው ሳይሆን ሆን ብሎ በመተው ነው። እግዚአብሔር ምሕረት ካደረገልን በኋላ ለበደላችን ተጠያቂዎች አያደርገንም እንጂ እርሱ ያለፈውንና የሚመጣውን ሁሉ ያውቃል። ከልባችን የሆነ እውነተኛ ንስሐ ስንገባ እግዚአብሔር በበዳላችን ምክንያት በእኛ ላይ ሊመጣ ያለውን ፍርድ/ቅጣት ይተዋል። ከዚያም በላይ ከእኛ ጋር መልካም ግንኙነትን ይጀምራል። አንድ ሰው በደል ፈጽሞ ፍርድ ቤት ቀርቦ በጉዳዩ ላይ ፍርድ ከተሰጠበት በኋላ የዚያ ሰው ፍርድ የተጠናቀቀ ቢሆንም መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ይመለሳል እንጂ አይደመሰስም።

ተበዳይ ለበዳይ ከልብ የሆነ ይቅርታ ቢያደርግም የበደል ትውስታ ከአእምሮ ውስጥ ላይሰረዝ ይችላል። ተበዳይ እነዚህን ክፉ ድርጊቶች አልፎ አልፎ ያስታውሳቸዋል። በተለይ የተፈጸመው በደል ክፋት ጥልቀት ያለውና በዚህም ተበዳይ የተጎዳው በከፍተኛ ሁኔታ ሲሆን ድርጊቱ ቶሎ ከአእምሮ አይረሳም። ተበዳይ በደሉ ስተፈጸመ በኋላ በተደጋጋሚ ሲያሰላስል ስቆየ መረጃው ወደ ትውስታ ውስጥ ገብቶ ሥፍራ ይይዛል። መረጃው ከጊዜ ርዝመት የተነሳ ሊረሳ የሚችል ቢሆንም አንዳንድ ትዝታ የሚቀሰቅሱ



ሁኔታዎች ሊከሰቱ ማስታወሱ አይቀርም። በተለይም ተበዳይ በሌሎች ሰዎች በሚበደልበት ወቅት በተመሳሳይ ስሜት ውስጥ ስለሚሆን በሌሎች ሰዎችም የደረሰበትን በደሎች ሁሉ የማስታወስ ዕድሉ ይበላል።

*ዳንኤልና ተስፋዬ በአንድ መንደር ውስጥ የሚኖሩ አብሮ አደጎችና ስጣም የሚዋደዱ ጓደኛሞች ነበሩ። ዳንኤል ከደሃ ቤተሰብ የተወለደ ሲሆን ተስፋዬ ግን በአካባቢው ደህና ገቢ አላቸው ከሚባል ቤተሰብ የተወለደ ነው። ሁለቱም ስትምህርት ቤት ውስጥ የታወቁ ጎበዝ ተማሪዎች በመሆናቸው በመምህራኖቻቸው የሚወደዱ ነበሩ። ከዕለታት አንድ ቀን በሠፈር ውስጥ ከሚገኙ ተደባዳቢ ልጆች መካከል አንዱ ተስፋዬ ከትምህርት ቤት ብቻውን ሲመለስ አይቶ ያዘውና ሁለት መቶ ብር ካላመጣህ አንገትህን እቆርጣለሁ ብሎ ያስፈራራዋል። ተደባዳቢው ልጅ በዕድሜ እጅግ ስለሚበልጥና ክፉ ድርጊቱንም ስለሚያውቅ ተስፋዬ «እሺ አመጣልሃለሁ» ብሎት ወደ ቤት ይሄዳል። ወደ ቤት እንደገባም ለእናቱ ምንም ሳይናገር ከእርስዋ ቦርሳ ውስጥ የተባለውን ገንዘብ ሰርቆ ለልጁ ይሰጠዋል።*

*በሚቀጥለው ቀን ተስፋዬ ዳንኤልን ወደ ቤቱ ለምሳ ይጋብዘውና አብረው በልተው እንደ ልማዳቸው ከሰዓት በኋላውን በጋራ ሲያጠኑ ውለው ዳንኤል ወደ ቤቱ ይመለሳል። የሚቀጥለው ቀን የገበያ ዕለት ስለነበር የተስፋዬ እናት ለቤት የሚያስፈልገውን ምግብ ለመግዛት ወደ ገበያ ለመሄድ ቦርሳዋን እንስታ ስትመለከት ያስቀመጠችው ገንዘብ የለም። በድንጋጤ ስሜት ሆና ተስፋዬን «ከዚህ ቦርሳ ውስጥ ገንዘብ አንስተህ ነበር ወይ?» አለችው። ተስፋዬም «እኔ ምንም አላየሁም» በማለት በድፍረት መለሰላት። እናትም ቀጠለችና «ትናንት እዚህ ቤት የመጣ ሰው ነበርን?» አለችው። ተስፋዬም «አዎን ዳንኤል እዚህ ነበር። ሠራተኛዋ ምሳ ሰጥታን አብረን በልተን ከዚያም ስንጫወት ነበር» የሚል መልስ ሰጣት። እርስዋ ተጨማሪ ነገር ከመናገሯ ቀድሞ ብሎ «ትናንት እዚህ አካባቢ ቆሞ ቦርሳውን ሲነካካው አይቼ ነበር» በማለት ዳንኤል ገንዘቡን እንደ ሰረቀ የሚያሳይ ፍንጭ ሰጣት።*

*የተስፋዬ እናትም በሁኔታ በጣም ተቆጣች። በገበያ ዕለት የዳንኤል አባት ደግሞ አንዲት የበግ ጠቦት ሽጦ ቆንጆ ሸሚዝ ገዝቶለት ነበር። የተስፋዬ እናት ወደ ትምህርት ቤት በመሄድ ስርዕሰ መምህሩ ዳንኤል አደረገ ብላ ያሰበችውን ነገር ነገረችው። ተስፋዬም ሁኔታው ትክክል እንደሆነ በመመስከር የዳንኤልን ጥፋተኛነት አረጋገጠ። ርዕሰ መምህሩና መምህራን ስሆነው ነገር ቢያዝኑም ለሌሎች ተማሪዎች ትምህርት ይሆን ዘንድ ዳንኤልን በተማሪዎች ሁሉ ፊት ገረፋት። ዳንኤል ሲገረፍ ገንዘቡን የወሰደውም ልጅ ቆሞ ያይ ነበር። ምንም ክፉ ማድረግ ልማዱ ቢሆንም ዳንኤል ባላጠፋ ነገር እንዲህ መቀጣቱ ስጣም አሳዝኖታል። ያን ዕለት ማታ ከተሰማው ሐዘን የተነሣ እራቱን ሳይበላ ነበር ያደረው።*

*ዳንኤል በአካሉ ላይ ከደረሰው ጉዳት በላይ በተማሪዎች ፊት በመደብደቡ የተሰማው የስሜት መሸማቀቅ እጅግ ጎዳው። ከዚህም በላይ ከተስፋዬ ጋር የነበረው ጓደኝነት ተቋረጠ። ከሌሎች ጋር ጓደኝነት*

*እንዳይመሠርት ደግሞ አሁን ሁሉም ተማሪ እንደ ሌባ ይመለከተዋል:: ወደ ሌላ ትምህርት ቤት ለመሄድ ምንም አማራጭ ስላልነበረው ትምህርቱን ቀጠለ:: እንደ ቀድሞ ጊዜው እያጠና በትምህርቱ ጥሩ ውጤትን ማምጣት ቀጠለ:: የእርሱ ባሕርይ ባለመለወጡ መምህራንና የክፍል ተማሪዎችም ይገረሙ ነበር::*

*ዳንኤል የመጀመሪያ ትምህርቱን ጨርሶ ወደ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ሲገባ ያ ተደባዳቢው ልጅ በውስጡ የተፈጠረው ሐዘን እያደገ በመምጣቱ የአእምሮ እረፍት ማግኘት አለብኝ ብሎ በማሰብ ሁለት መቶ ብር ይዞ ወደ ተሰፋዬ እናት ይሄዳል:: በዕለተ ሰንበት የሠፈር ሰዎች አንድ ላይ ተሰብስበው ቡና እየጠጡ ሳለ መጣና በተሰፋዬ እናት ጉልበት ላይ ወድቆ «እባክሽን ይቅር በይኝ! ሁለት መቶ ብሩን የወሰድኩት እኔ ነኝ» በማለት የሆነውን ነገር ሁሉ ነገራት:: ያየውና የሰማው ሁሉ በዚያው ፈዝዞ ቀረ:: የተስፋዬ እናት የለማችውን ነገር ማመን አቃታት:: ሁሉም ዳንኤል ጥፋተኛ እንዳልሆነ አወቁ:: በትምህርት ቤት የደረሰበት ቅጣትና በሠፈር እንደ ሌባ መታየቱ አሳዘናቸው:: ተሰፋዬ ያደረገው ነገር ትክክል እንዳልነበረ መናገር ጀመሩ::*

*የተሰፋዬ እናት ከልጇ ጋር ወደ ዳንኤል ቤተሰብ ሄደች:: ወላጆቹና እርሱ ባሉበት ሥፍራ የሆነውን ሁሉ በመናገር ዳንኤልን ይቅርታ ጠየቀች:: ዳንኤልም እውነቱ አንድ ቀን ሊወጣ ይችላል በሚል አሳብ ነገሩን እንደ ተወው በመናገር ይቅር አላቸው:: ከተሰፋዬም ጋር ተሳሳሙ:: አሁን ሁለቱም አድገው ትልቅ ሰው ሆነዋል:: ነገር ግን ሁለቱም የሆነውን ነገር ያስታውሱታል:: ተስፋዬ እንዲህ ያለውን ነገር በመፈጸሙ አሁንም አልፎ አልፎ የበደለኛነት ስሜት ይሰማዋል:: አንዳንዴ ደግሞ በራሱ ላይ ይስቃል:: ዳንኤልም አንዳንድ ጊዜ ጥፋተኛ ያልሆነ ሰው ሰዎች ጥፋተኛ እንደሆነ በሐሰት ቢመሰክሩበት ያልተገባውን ቅጣት ይቀበላል:: ከዚህ በኋላ እውነቱ ቢወጣ ምን ዋጋ ይኖረዋል? እያለ ያስባል:: በአእምሮአቸው ውስጥ በወጣትነት ጊዜ የተከናወነው ነገር ትናንት እንደሆነ ዓይነት ትኩስ ነው::*

በደልን ስለማስታወስ ጳጳስ ዴስሞን ቱቱ «ሰዎች ይቅርታ በሚያደርጉበት ጊዜ ሁኔታውን እንዲረሱ አይጠየቁም:: ከመርሳት ይልቅ ማስታወስ እነዚያ እሰቃቂ፣ ጭካኔና ግፍ የተሞሉባቸው የጥቃት ድርጊቶች ዳግመኛ እንዳይከሰቱ ይረዳል» ብለው ተናግረዋል::[6] በዚህ አሳብ መሠረት ተበዳዮች ይቅርታ ሲያደርጉ በእነርሱ ላይ የደረሰውን በደል እንዲረሱ መጠየቅ ትክክል አይደለም:: እነርሱ ብቻም ሳይሆን በዳዮችም ያደረጉትን ክፉ ድርጊት መርሳት የለባቸውም:: ሁለቱም ወገኖች የተፈጸመው በደል ዳግመኛ እንዳይከሰት ለማድረግ ታሪኩን ማስታወሳቸው ያግዛል:: በደልን ይቅር ካሉ በኋላ በደሉን አለመርሳት ጥቅም ያለው በመሆኑም ሆን ብሎ ማስታወስ የበለጠ ጥቅም እንዳለው ያሳስበናል::

[6] Tutu, D. P.271



በደልን ማስታወስ ከይቅርታ በፊትና በኋላ ይለያያል:: በግንኙነት ውስጥ በደል ተፈጽሞ ይቅርታ ከመደረጉ በፊት ተበዳይ በደሉን ሲያስብ ወደ እእምሮው የሚመጡ መጥፎ የሆኑ ስሜቶች ናቸው:: በዳይን ለመበቀል ያስባል:: ከትውስታው ጋር የሚመጡ እነዚህ ስሜቶች ግንኙነቱንና ተበዳይን የሚጎዱ ይሆናሉ:: ከይቅርታ በኋላ ያለፈውን በደል ማስታወስ ማለት እነዚህን አሳቦች ማስተናገድ አይደለም:: ሰዎች ከልባቸው ይቅርታ በሚያደርጉበት ጊዜ በሕይወታቸው ላይ አንድ ጊዜ የተፈጸመውን በደል እያሰላሰሉ አይኖሩም:: ወደ ትውስታ የሚመጡ አሳቦች ቀስ በቀስ እየቀሩና በተበዳይ ሕይወት ላይ የሚኖራቸውም አሉታዊ ተጽዕኖ እየቀነሰ ይመጣል:: ጌሪ ኮሊንስ የተባሉ ክርስቲያን የሥነልቦና ምሁር «በቅድሚያ ይቅርታ ይመጣል፣ ከዚያም ያለፈውን በደል ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል መርሳት ተከትሎ ይመጣል» በማለት ተናግረዋል::[7]

እንዳንድ ጊዜ በሰዎች የደረሰብንን በደል ለመርሳት በምናደርገው ትግል ውስጥ ያንን በደል ከመርሳት ይልቅ በደሉን ይበልጥ እያስታወስን እንሄዳለን:: ስለዚህ በስብዓዊ ግንኙነቶቻችን ውስጥ የተፈጠረው ችግር ሳይፈታ (በእኛና በሌሎች መካከል የተፈጠረው በደል ሳይስተካከል) እንዲሁ ሁኔታውን ለመርሳት ጥረት ማድረግ ሁኔታው በሚገባ በአእምሮ ውስጥ እንዲቀረጽ ሁኔታዎችን ማመቻቸትን ያመጣል:: አንድ ነገር በአእምሮ ትውስታ ውስጥ ገብቶ መታወስ የሚችልበት ሥፍራውን መያዝ እንዲችል ሁኔታውን ደጋግሞ ማሰላሰል እንደሚረዳ ሁሉ በዚህ ጉዳይም በደሉን ለመርሳት በምናደርገው ትግል ሳናውቀው ጉዳዩ በአእምሮአችን ውስጥ እንዲሰርጽ እናደርጋለን::

አንዳንድ ሰዎች ተበዳይን በሚያገኙበት ጊዜ የደረሰበትን በደል እንዲረሳው ይመክሩታል:: «እባክህን እርሳው» ይሉታል:: እንዴት አድርጎ የተጎዳበትን ነገር መርሳት ይችላል? ትክክለኛ መርሳት ከእውነተኛ ይቅርታ በኋላ የሚመጣ ውጤት እንጂ ይቅርታን ለማምጣት እንደ መሣሪያ የሚያገለግል ክስተት አይደለም:: ስለዚህ ሁኔታውን ተገቢ በሆነ መንገድ ለመፍታት ከመሞከር ቀደም ብሎ እንዲሁ ለመርሳት ጥረት ማድረግ ውጤት አይኖረውም:: በግንኙነት ውስጥ የተፈጠረውን ጉዳይ ለመፍታት ጥረት ቢደረግ አንድ ሰው ስለበደሉ የሚሰማው ስሜት ትኩሳት ቀስ በቀስ ይቀንሳል:: በእርግጥ አንዳንድ ነገሮችን ከማስታወስ ይልቅ መርሳት ጠቃሚ እንደሆነ ቢታሰብም በሕይወት ጉዞ አደገኛ የሆኑትን ነገሮች መርሳት የሚቻል አይመስለኝም::

ካለፈው ሕይወቱ ራሱን መለየት የሚፈልግ ሰው የወደፊት ነገር አይታየውም:: ሰዎች ያለፈው ነገር እንዲሁ ከንቱ ሆኖ ወይም ያለፈ ነገር ብቻ ሆኖ እንዲቀር ማድረግ የሚያስችለው የንስሐ ዓይነት ነው:: በቀድሞ ሕይወታቸው ዘመን የተፈጸሙ ሆነው የዛሬውን ሕይወታቸውን በተገቢው

[7] Collins, G.R. (1988). *Christian Counseling.* W Publishing. P. 145

ሁኔታ እንዳይመሩ እንቅፋት የሚሆኑባቸውን ማስወገድ ነው። በማንኛውም ሰው ሕይወት ያለፈው ነገር በረከትና መርገም የሆኑ ነገሮች ይኖረዋል።[8]

በይቅርታ ሂደት ከታለፈ ካለፈው ሕይወት ውስጥ መርገሙን በመተው በረከቱን ለዛሬም መጠቀም ይቻላል። ይቅርታ ማድረጉ ያለፈው ክስተት የዛሬውን ሕይወት በአሉታዊ መንገድ እንዳይመራ የሚከላከል መሣሪያ ነው። በቀደመው ሕይወት የተፈጠረው መርዝ የዛሬውን ሕይወት እንዳይመርዝ ገደብ መሥራት ነው። ለበዳይ ይቅርታ ማድረግ ያለፈው ክስተት የሚታይበትን እይታ ወይም የሁኔታውን ትርጉም ይለውጣል። በዚህ ሂደት ውስጥ ደግሞ ይህ ያለፈው ነገር በወደፊት ሕይወት ላይ የሚኖረውም ተጽዕኖ እንዲሁ ይለወጣል። ይቅርታ እንደ ወንፊት ነው:- ካለፈው ሕይወታችን ከእኛ ጋር መቀጠል የሚገባቸውን ጠቃሚ ነገሮች ያጠራልናል። ከዚያም ጠቃሚ የሆኑት ትምህርቶች ይዘን ሕይወታችንን እናንጽበታለን።

ማጠቃለያ:

- ለበዳይ ይቅርታ ማድረግ የተፈጸመው በደል በተበዳይ ላይ ሲደረግ የተገባ ነገር መሆኑን ማጽደቅ አይደለም።
- ይቅር ባይነት በተበዳይ ተከታታይነት ባለው ሁኔታ ለመጠቃት ራስን ማጋለጥ አይደለም።
- ለበዳይ ይቅርታ ማድረግ ለእርቅ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ቢችልም በራሱ እርቅን ሊወክል አይችልም።
- ተበዳይ በእርሱ ላይ የተፈጸመውን በደል ከይቅርታ በኋላ ወዲያውኑ እንዲረሳ መጠበቅ ትክክል አይደለም። ይቅርታ የበደል መርሳትን ላያስከትል ይችላል።

የማሰላሰል ጥያቄዎች:

(1) ይቅርታ በበደል ምክንያት የፈረሰውን ግንኙነት ማደስ ካልቻለ ይቅርታው ሙሉ ሆኗል ማለት ይቻላል? ለምን?

(2) «በዳይን መቻል ገደብ ሊኖረው ይገባል» የሚለው አሳብ በሁኔታዎች ላይ ባልተመሠረተ ፍቅር መዋደድ አለብን ከሚለው አሳብ ጋር እንዴት ይጣጣማል?

(3) በሕይወትህ ከተለማመድከው ሁኔታ በመነሳት «ይቅርታ ምን አይደለም?» ለሚለው ጥያቄ ምን መልስ ትሰጣለህ?

[8] Klassen, p.209-213



# 2
# ይቅርታ ምንድነው?

የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ይቅርታን «የሰውን ንብረት፣ መብትን ወይም ክብርን ከማጉደል እንዲሁም የሞራል ሕግን ከመጣስ ከሚመጣው በደል የተነሣ የማስማን የቁጣ ስሜት መተው» በማለት ይተረጉማል። ከዚህም ጋር በማያያዝ ለይቅርታ ንስሐ መግባትና ለተፈጸመው በደል ቤዛ ወይም ካሣ ለመክፈል ፈቃደኝነቱ መኖር አለበት። በዚህ ሁኔታ በሚመጣ ይቅርታ የሚገኘው ውጤት ደግሞ የሁለቱም ወገኖች ቀድሞ የነበረው ግንኙነት መታደስና ኅብረታቸውን በአዲስ ሁኔታ መቀጠል እንደሆነ ያብራራል።[9]

በዚህ አሳብ መሠረት ሰብዓዊ ግንኙነትን ማበላሸት የሚችለው በደል ሊከሰት የሚችልባቸው አራት መሠረታዊ ነገሮች ተጠቅሰዋል። እነርሱም የሰውን ንብረት ያለባለቤቱ ፈቃድ መጠቀም ወይም ያለ አግባቢ መያዝ፣ የሌላውን ሰው መብት በማንኛውም መንገድ መጣስ፣ የሰዎችን ክብር በቃልም ሆነ በድርጊት መንካትና ማጉደል እንዲሁም በሕሊና ውስጥ የተጻፈውን የሞራል ሕግ ጥሶ በማለፍ ተገቢ ያልሆነ ነገርን በሰዎች ላይ ማድረስ ናቸው።

ይቅርታ የበቀልን አሳብና እርምጃን መተው ነው

በእነዚህ ዓይነት መንስኤዎች የሚመጣው በደል ደግሞ ከተበዳይ ላይ የሚያስከትለው የቁጣ ስሜት እንደሆነ ይገልጻል። እንግዲህ አንድ ሰው ይቅርታ አደረገ የሚባለው ሰዎች በእርሱ ንብረት፣ መብት፣ ክብር ወይም ሞራሉ ላይ በደል በሚያደርሱበት ጊዜ በውስጡ የተሰማውን የቁጣ ስሜት ሲተው ነው።

ይቅርታ ማለት እኛን ለበደሉን፣ በእኛ ላይ ጥፋት ለፈጸሙ ወይም እኛን ለከፉ ነገር አሳልፎ ለሰጡ ሰዎች የሚሰማንን የበቀል አሳብና ፍላጎታችንን ማስወገድ ነው። ዘላቂነት ባለው ግንኙነት ውስጥ ሰዎች በድለውን በውስጣችን የተሰማንን መጥፎ ስሜቶች ማስወገድ ብቻ በቂ አይደለም። ይቅርታ ከበደሉ የተነሣ የተሰማንን አሉታዊ ስሜቶችን ከማስወገድ ያልፋል። በዳይን ለመበቀል የሚገፋፋንን ስሜት ማርገብና ከዚያ ሰው ጋር እንደገና ግንኙነት እለማድረግ የሚፈልገውን አሳባችንን መተውን ይጨምራል። በዳይ ያደረገው በደል ጎጂ እንደሆነ ቢታወቅም በተጨማሪም ከበደሉ የተነሣ ሕይወታችን ቢጎዳም ከዚያ ሰው ጋር መልካም ግንኙነት ለመመሥረት በተስፋ መጓዝ መቻል ነው። ይቅርታን በዚህ ሁኔታ ስንመለከት ከበደል የተነሣ የተሰማንን መጥፎ ስሜቶችን በማስወገድ በእነርሱ ፈንታ ደግሞ መልካም የሆኑ ስሜቶችን መተካት ነው።

[9] Douglas & Tenney (1987). *Bible Dictionary*. Zondervan Corporation. P. 360

እንግዲህ ይቅርታ በሰብዓዊ ግንኙነት ውስጥ በደል ከተፈጸመ በኋላ በተበዳይ ሕይወት ውስጥ የሚመጣ የአቋም ለውጥ ነው:: ተበዳይ ለበዳይ ይቅርታ በሚያደርግበት ጊዜ በሕይወቱ ውስጥ በዳይን ለመበቀል የሚኖረው የልብ መነሳሳት ይቀንሳል፣ ከእርሱ ጋር ላለመገናኘት የሚያደርጋቸውን ጥረቶችን ይተዋል እንዲሁም ቀድሞ የነበረውን ግንኙነት እንደገና በማደስ መቀጥል ይፈልጋል::

እነዚህን መጥፎ ስሜቶች በማስወገድ የመጀመሪያ ተጠቃሚ ተበዳዩ ሰው ነው:: ይህን የበቀል ስሜትና ፍላጎትን ማስወገድ ውስጣዊ የልብ ሰላምን ይመልሳል:: ከዚህም በተጨማሪ የተበዳዩ ሕይወት በተፈጸመው በደልና በደረሰው ቁስል እንዳይታይና እንዳይተረጎም ነጻነትን ይሰጣል:: ሰዎች በእኛ ላይ የፈጸሙት በደል የሕይወታችንን አቅጣጫ እንዳይወስን አሻፈረኝ ማለት ተገቢ ነው:: በእኛ ላይ የደረሰውን በደል ብቻ በማሰብ ለሌሎች ማለብና መሥራት የሚገባንን መልካም ተልዕኮዎች ከግብ ሳናደርስ እንዳንቀር ለበዳይ ባሪያ ከመሆን ነጻ መውጣት ነው::

*ይቅርታ ስለተፈጸመው በደል ንስሐ መግባትና ካሣ ለመክፈል ፈቃደኛ መሆን ነው*

ይቅርታ ሙሉ እንዲሆን በዳይ ማድረግ የሚገባቸው ነገሮችም ተጠቅሰዋል:: በዳይ በተበዳይ ላይ ያደረሰው በደል ተሰምቶት ንስሐ መግባት ይኖርበታል:: በዳይ ጥፋቱን በማመንና የተጠያቂነት ስሜት ተሰምቶት ላደረሰው በደል ተበዳይ ይቅር እንዲለው መጠየቅ ይጠበቅበታል:: ሆኖም ይህ ሁልጊዜ የሚደረግ ላይሆን ይችላል:: በድሉ ይቅርታ መጠየቅ የሚጠበቅ ጉዳይ ቢሆንም በዳይ ዘወትር ለፈጸመው በደል ይቅርታ ይጠይቃል ማለት አይደለም::

እንደ ሌውስ ቢ ስሜዴስ አገላለጽ ንስሐ መግባት እራት ዋና ዋና ደረጃዎች አሉት:: እነዚህ ደረጃዎች ተከታታይነት ያላቸው ሆነው እራተኛው ደረጃ ሲያልቅ ንስሐ ተከናወነ ማለት ይቻላል:: እነዚህም ደረጃዎች በሚከተለው ሁኔታ ተብራርተዋል::

❖ *መገንዘብ:-* በዳይ ራሱን በተበዳይ ሥፍራ በማስቀመጥ የሆነውን ነገር በተበጻይ እይታ ማየት መቻል ነው:: ከበደሉ የተነሣ በተበዳይ ሕይወት ላይ የደረሰውን ይገነዘባል:: ይህም ብቻ ሳይሆን ተበዳይ ደረሰብኝ ብሎ የሚናገራቸው ነገሮች እውነት መሆናቸውን ይረዳል:: በአእምሮው በተበዳይ አእምሮ ውስጥ ያሉትን አሳቦች ይካፈላል::

❖ *ስሜትን መጋራት:-* ከበደሉ የተነሣ ተበዳይ ምን ያህል ሕይወቱ እንደተጎዳና ምን ያህል የስሜት ሰቃይ ውስጥ እንደገባ በመገንዘብ ስሜቱን መጋራት ይጀምራል:: በአእምሮ ከመረዳትም አልፎ በተበዳይ ልብ ውስጥ ያለውን ስሜት መካፈል ይከስታል:: በዳይ በተበዳይ ላይ ይህን የሚያህል



የስሜት ኪሣራ እንዲመጣበት ምክንያት በመሆኑ የበደለኛነት ስሜት ይሰማዋል:: ለፈጸመውም በደል «ፍርድ» እንደሚገባው ይቀበላል::

❖ *መናዘዝ:-* በዳይ በተበዳይ ላይ ያደረሰው ጉዳት እንደ ተረዳና ስሜቱንም እንደ ተካፈለ በግልጽ መናገር ይጀምራል:: ይህ መናዘዝ «እኔ ጥፋተኛ ነኝ» ከማለትም ያለፈ ነው:: አንዳንድ ጊዜ ሰዎች የፈጸሙት በደል ያደረሰውን ጉዳት በመገንዘብ ወይም የተበዳይን ስሜት ሳይጋሩ በደላቸው ሊያመልጡት የማይችሉት ነገር በመሆኑ ጥፋተኛ መሆናቸውን መናገር ይችላሉ:: እውነተኛ መናዘዝ ለበዳይና ለተበዳይ የሕይወትና የግንኙነት ፈውስ ለማምጣት እንጂ ሁኔታውን ለማርገብ ብቻ እንደ መማለጃ ለተበዳይ ወይም ሁኔታውን ለሚከታተል አካል መስጠት አይደለም:: ከልብ የሆነ መናዘዝ ፈውስን ያመጣል:: ስለዚህ በዳይ የተበዳይን ይቅርታ ማግኘት ለሕይወቱ ፈውስ አስፈላጊ መሆኑን በመናገር ምሕረትን ይጠይቃል::

❖ ተስፋ *መስጠት:-* የተፈጸመው በደል ያስከተለውን የሕይወት ኪሣራ በመገንዘብ ወደፊት ተመሳሳይ ዓይነት በደል በተበዳይ ላይ ላለመፈጸም ቃል መግባት ነው:: ይህ ተስፋ እውን የሚሆነው ወደፊት በሚሆኑ ጉዳዮች በመሆኑ ከወዲሁ እርግጠኛ መሆን አይቻልም:: ሆኖም ግን የበዳይ መናዘዝ ምን ያህል እውነተኛ እንደሆነ በሚሰጠው የተስፋ ቃል መገመት ይቻላል::

በግል ሕይወት ተግባራዊ ለማድረግ ለሰው ልጅ ከሚከብዱ ነገሮች አንዱ ከልብ የሆነ እውነተኛ ንስሐ መግባት ነው:: «እኔ ጥፋተኛ ነኝ» ብሎ በሰው ፊት መናገር እጅግ ከባድ ይሆናል:: ማንኛውም ሰው ጥፋተኛ መሆኑን አምኖ ለመቀበል ይቸገራል:: በመሠረተ አሳብ ማንኛውም ሰው ስህተት ሊፈጽም እንደሚችል ብዙዎች ቢያውቁትም በራሳቸው ላይ ሲደርስ ግን ተግባራዊ ማድረግ ብዙዎችን ሲቸግራቸው ይስተዋላል:: በአብዛኛው እንዱ የፈጸመውን በደል በቀጥታ ከማመን ይልቅ ያንን ስህተት የፈጸመበትን ምክንያት መዘርዘር ይፈልጋል:: ስህተት ለምን እንደ ተፈጸመ መግለጽ በራሱ ክፋት ባይኖረውም እንዲህ ማድረግ ንስሐ ከመግባት ይልቅ ራስን ለመከላከል የሚወሰድ እርምጃ እንደሆነ ስለሚታሰብ ግንኙነትን ለማደስ የሚኖረው ሚና አነስተኛ ነው:: እውነተኛ ንስሐ መግባት በደሉ የተፈጸመበትን ምክንያት ከመግለጽ፣ ሌሎች ሰዎችንም በደለኞች እንደሆኑ ከመናገር ይልቅ ስህተታችንን እውነት መሆኑን በማመን ለተፈጸመው በደል ተጠያቂዎች እንደሆንን መቀበል ነው::

በሰብዓዊ ግንኙነት ውስጥ በደል ሲፈጸም «ይህን በደል የፈጸምኩት እኔ ነኝ» ብሎ በድፍረት መናገር በአንድ በኩል ራስን «ለጥቃት» አሳልፎ መስጠት ነው:: በግንኙነት ውስጥ ያሉ እንዲሁም ከውጭ ሆነው የሚያዩ ተመልካቾች የግንኙነት ችግር መንስኤው እኛ እንደሆን በግልጽ በማወቅ ጣታቸውን በእኛ ላይ ይቀስራሉ:: እነርሱም ቢሆኑ ስህተት መፈጸም የሚችሉ ዓይነት ሰዎች ሆነው ሳሉ ጥፋታችንን በማመናችን እኛን እንደ ጭራቅ የማየትና የመኮነን ባሕርይ ይታይባቸዋል:: በሌላ በኩል ደግሞ በውስጣችን ያለውን አሳብና ስሜታችንን እንዲሁም የራሳችንን ድርጊት በግልጽ በመናገር ከእውነት ጋር ለመታረቅ ወደ ብርሃን በመውጣታችን

ነፃነት ይለማናል። በጨለማው ውስጥ ከበደል ጋር በአስራት ከመኖር ይልቅ የራስን ትክክለኛ ድርጊት በመግለጽ ወደ ብርሃን ወጥቶ በነፃነት መኖር ለራስም ሆነ ከተበዳይ ጋር ለሚኖረው ግንኙነት የተሻለ ውጤት አለው።

አንድ ሰው በሰዎች ላይ ካደረሰው በደል መማር የሚችለው የፈጸመውን ነገር አምኖ ሲቀበል ነው። በደል የፈጸመ ሰው በደል የፈጸመበትን የራሱን ውስጣዊ ምክንያት መደርደር ወይም በሁኔታዎች ግፊት እንደፈጸመው በመናገር ሌሎች ነገሮችን ተጠያቂ ለማድረግ በሚነሳበት ጊዜ ስለህተቱ ሊማር የሚገባውን ተገቢ ትምህርት ከመማር ራሱን እያራቀ ይገኛል። አንድ ሰው በደሉን በራሱ ብቻ የፈጸመ ባይሆንም እንኳ ሌሎችን ከመኮነን ይልቅ ሁኔታውን ቢቀበል ለራሱም የሚማረው ትምህርት ስመኖሩም በተጨማሪ ከተበዳይ ጋር የሚኖረው ግንኙነት በአዎንታዊ መልኩ ይለወጣል። ጥበብና ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላቸው ሰዎች እምብዛም ሳይቸገሩ ስህተታቸውንና በሰዎች ላይ ያደረሱትን በደል ይቀበላሉ። ከዚህም የተነሣ ስለህተታቸው ለሚቀጥለው ሕይወታቸው የሚማሩት መልካም ቁም ነገር ይኖራል። ተበዳዮችንም ይቅርታ ለመጠየቅ አይቸገሩም።

በተፈጥሮ ተግባራዊ ለማድረግ ከባድ የሆነው በዳይን ይቅር ማለት ቀላል የሚሆነው በዳይ ስላደረሰው በደል በቀጥታ ንስሐ ሊገባ ነው፡- «እኔ እንዲህ ዓይነት በደል ፈጽሜአለሁ፣ ለዚህም ተጠያቂ ነኝ» ማለት መቻል ነው። ከልቡ ተስምቶት ጥፋተኛ መሆኑን ካመነ፣ ተበዳይ ይቅር ከማለት በስተቀር ምን አዎንታዊ የሆነ እርምጃ መውሰድ ይችላል? በዚህ ዓይነት ልብ ወደ እኛ ለሚመጡ ሰዎች ከልብ የሆነ ይቅርታ ማድረግ በበደሉ ምክንያት የደረሰውን ቁስል ለመፈወስና ከተበዳይም ጋር ኅብረትን በጤናማ መንፈስ ለመቀጠል ያግዛል።

በዳይ በቃል ብቻም ሳይሆን እንደ አስፈላጊነቱ ለተበዳይ ካሣ መክፈል ይገባዋል። ካሣ ተበዳይ በደሉ ባይደርስበት ኖሮ ሊኖረው የሚችለውን ሁኔታ ሊመልስለት የሚችለውን ተመጣጣኝ ክፊያ መክፈል ነው። ይቅርታ መጠየቅና ከተበዳይ ይቅርታን ማግኘት ለተበላሸው ነገር ካሣ መክፈልን ሳያስቀር ይችላል።

ካሣን ከበዳይ መቀበል ምን ያህል መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት አለው? የሚለውን እሳብ በተመለከተ የተለያዩ እሳቦችን እናገኛለን። በብሉይ ኪዳን አንድ ሰው የሌላውን ሰው ንብረት ከሰረቀ ያንን ንብረት መክፈል እንዳለበት የሚደነግግ ሕግ ነበር። «ሌባ የሰረቀውን መክፈል አለበት፣ ምንም ከሌለው ግን የሰረቀውን ይክፍል ዘንድ ይሸጥ» (አ.መ.ት.) (ዘጸ22:3) ይላል። በዚህ ቃል መሠረት የሰውን ንብረት ያለ አግባብ የወሰደና የተጠቀመበት ሰው የንብረቱን ባለቤት «በድየአለሁና ይቅር በለኝ» ማለቱ ብቻ በቂ አይደለም። ያለ አግባብ የወሰደውን ንብረት መመለስ አለበት። እንዲያውም መጀመሪያ ከወሰደው ጨምሮ መክፈል እንደሚጠበቅበት ታዟል። ይህ ሰው ለተበዳይ መክፈል የሚያስችለው አቅም (ሀብት ወይም ንብረት) ባይኖረው በትጋት



በመሥራት ዕዳውን መክፈል ይገባዋል። በአንደበት ብቻ ንስሐ ገብቻለሁ ብሎ በአቋራጭ የማምለጫ መንገድ የለም።

የሰውን ንብረት ያለ አግባብ የወሰደው ሰው ለባለንብረቱ ለመመለስ ከልብ የሆነ ፈቃደኝነት በሚኖርበት ጊዜና ተበዳይን ይቅርታ መጠየቁም በደሉ ሊያስከትል ከሚችለው ቅጣት ለማምለጥ ብቻ ብሎ ሳይሆን በፈጸመው በደል ከልቡ በማዘኑ መሆኑ ከታወቀ ተበዳይ ምሕረት ሊያደርግለትና ካሣ መቀበልን ሊተው ይችላል።

አንድ ሰው የሌላውን ሰው ንብረት ያለ አግባብ በመጠቀሙ ካሣ መክፈል ይችላል። በገንዘብና በቁሳ ቁስ የማይገመትን በደል ያደረሰውስ እንዴት ካሣን መክፈል ይቻላል? ለምሳሌ የሰውን ክብር ወይም መብትን ወይም ሞራልን የሚጎዳ ድርጊት ቢፈጸም ካሣውን እንዴት መገመት ይቻላል? ለምሳሌ ያህል አንድ ሰው በአደባባይ የሌላውን ሰብዓዊ መብት በመጣስ በሞራሉ ላይ በደል ቢፈጽም በዳይ ተበዳይን በአደባባይ ይቅርታ በመጠየቅ መካስ ይችላል። ይህ በወቅቱ የደረሰውን ሥነልቦናዊ ስብራትን መጠገን ባይችልም ተበዳይ በማሕበረሰቡ መካከል ያለው መልካም «ስም» ተጠብቆለት እንዲኖር ማድረግ ይችላል።

እውነተኛ ንስሐ መግባት ካሣ መክፈልን እንደማያስቀርም ከአዲስ ኪዳን አንድ ታሪክ እናገኛለን። ዘኬዎስ የሚባል ቀራጭ ከጌታ ኢየሱስ ጋር ተገናኝቶ ኃጢአቱን በተናዘዘበት ወቅት «ማንንም በሐሰት ስለሼ እንደሆንሁ አራት እጥፍ እመልሳለሁ» (ሉቃ19:8) ብሎ ተናግሮ ነበር። ሆኖም ይህን ያለውን ነገር እንዲከፍል ጌታ ኢየሱስ አሳዘዘውም። በዚህ ክፍል የተጠቀሰው ይቅርታ ሰው ንስሐ ሊገባ ከእግዚአብሔር ዘንድ ለሰው የሚሰጠው ምሕረት ነው እንጂ በሰብዓዊ ግንኙነት ውስጥ የሚጠበቅ ዓይነት አይደለም። ከእግዚአብሔር ዘንድ ንስሐ ገብቶ የኃጢአት ይቅርታ ማግኘት በሰብዓዊ ግንኙነት ውስጥ የተፈጸመውን በደል ለማስተካከል እርምጃ ለመውሰድ ያነሳሳል። እውነተኛ ንስሐ ገብቶ የኃጢአት ይቅርታን ማግኘት ትክክለኛውን ነገር በተለይ ደግሞ በቃሉ ውስጥ የተጠቀሰውን መልካም ነገር ለማድረግ ያበረታታል እንጂ በጎውን ነገር ከመፈጸም አይከለክልም። «ይቅርታ ትክክለኛ የሆነውን ነገር ከማድረግ አያስቀርም።»[10]

በእርግጥ በዳይ በተበዳይ ላይ ላደረሰው በደል ካሣ በመክፈል እንደ አመቺነቱ አስፈላጊ መሆኑ ቢታመንበትም ይህን እየጠበቁ በዳይን ይቅር አለማለት ግን ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል። ካሣን የሚጠብቅ ሰው በራሱ ማድረግ የሚችለውን ነገር ትቶ ሌላ ሰው ሊወስድ ባለው እርምጃ ላይ ጥገኛ ይሆናል። እንዲህ ሲሆን የተበዳይን እርምጃ የሚወስነው በዳይ የሚያደርገው እንቅስቃሴ ይሆናል። ይህ ደግሞ የግል ሕይወት ፈውስና ዕድገትን በሌሎች ሰዎች እርምጃ ላይ እንዲመረኮዝ ያደርጋል። በዳይ ካሣ እስከሰጥ ድረስ መጠበቅ የይቅርባይነት መንፈስ ማጣት ምልክት ነው። ይቅርታ ለማድረግ የማይፈልግ ሰው በአብዛኛው በዳይ ካሣ እስከንከፍለው ድረስ ይጠብቃል።

[10] MacArthur, John.

በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ በሚሆንበት ጊዜ ይቅርታ ማድረግ ብዙ ጊዜያትን ሊፈጅ ይችላል።[11] ስለዚህ ይቅርታ ለማድረግ በዳይ ካሣ እስኪከፍል ድረስ መጠበቅ የለበትም። ካሣ መክፈል የበዳይ ድርሻ በመሆኑ እርሱ ታስሮ ሕይወትን ከፈውስና ከዕድገት ማገድ የሚጠበቀው ካሣ ከሚያመጣው ጥቅም የበለጠ ኪሣራ ያስከትላል።

## ይቅርታ በበደል ምክንያት የፈረሰውን ግንኙነት ማደስ ነው

ይቅርታ ሁለቱን ባላተፈ መልኩ ሲካሄድ የበዳይና የተበዳይ ግንኙነትን ያድሳል። ሁለቱም የቀድሞ ኅብረታቸውን በማደስ በፊት ይኖሩ በነበሩበት ሁኔታ መኖር ይጀምራሉ። ይቅርታ ሲደረግ ግንኙነትን ማደስና አብሮ መኖር መጀመር ሁልጊዜ የሚመጣ ውጤት ላይሆን ቢችልም ከዚያ በኋላ ግን የሚጠበቅ መልካም ፍሬ ነው።

ይቅርታ እኛን በትክክለኛውና በተገቢው መንገድ ያስተናግደናል ብለን ያመነው ሰው በእኛ ላይ በደል ሲፈጽም የቀደመውን ኅብረት እንደገና ለማደስ የምንጠቀምበት የፍቅር ማደሻ መሣሪያ ነው። በዚህ እይታ መሠረት በአብዛኛው በደል የሚመጣው እኛ ከምናውቀውና ከምናምነው ሰው ነው። ከእኛ ሩቅ የሆነ ሰው ማለት ከእኛ ጋር የቅርብ ግንኙነት የሌለው እንግዳ የሆነ ሰው እኛን አይበድልም ማለት ሳይሆን እንዲህ ዓይነት ሰው ቢበድለንም እንኳ ብዙ አንጎዳበትም። ምክንያቱም እኛን በለማያውቀን፣ ሆን ብሎ እኛን ለማጥቃት ሳይሆን በድንገት ነው እንዲህ ዓይነት ከፉ ነገር የፈጸመብን ብለን ራሳችንን እናሳምናለን። ነገር ግን በደሉ በጣም የሚሰማን አንድ እኛን የሚቀርብና እኛ የምንደገፍበት ሰው ሲበድለን ነው። ስለዚህ ሕይወትን የሚያሳምም በደል የሚመጣው ከቅርብ ግንኙነት እንደሆነ እንመለከታለን።

እንግዲህ ይቅርታ በበደል ምክንያት የተሰበረውን የሰዎችን ውስጣዊ ሕይወት በመፈወስ በሰብዓዊ ግንኙነት ውስጥ የነበረው የቀድሞ ዓይነት ኅብረት እንዲመጣ መንገድ የሚጠርግ ድርጊታዊ እርምጃ ነው። ይቅርታ በሰዎች መካከል ያለውን ፍቅርና ስምምነት የሚያጠፋውን መርዝ በማጥፋት በግንኙነት ውስጥ ሁለንተናዊ ሙሉነትና መተማመን እንዲኖር አቅጣጫ የሚያሳይ ተግባር ነው።

## ይቅርታ ከፍቅር የተነሳ በዳይን መቀበል ነው

ይቅርታ ሰዎች እርስ በርሳቸው ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲቀበሉ ዕድል የሚሰጣቸው፣ ለተፈጸመባቸው በደል ከፉ ምላሽ እንዳይሰጡ የሚያደርግና ሌሎችን ለመውደድ እንቅፋት የሚሆኑትን ነገሮች የሚያስወግዱበት ከተፈጥሮ ባሕርይ በላይ የሆነ ድርጊት ነው። በዚህ አሳብ መሠረት ይቅርታ ሰዎችን ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ለመውደድ የሚያስችል

---

[11] Stanley, C.C. (2002). *The Gift of Forgiveness.* P. 9-10



መሣሪያ ነው። እያንዳንዱ ሰው በሌሎች ዘንድ ተቀባይነት ሊያስጠው የሚያስችል ጠንካራና ተወዳጅ ነገር እንዳለው ሁሉ ሌሎች ሰዎች የማይጠዱለትም ባሕርይ ይኖረዋል። በግንኙነት ውስጥ ደግሞ ሁለቱም ነገሮች- መልካሙና ከፉው ገጽታዎች ይገለጣሉ። በሰዎች ጠንካራ ጎን በኩል በረከት ወይም ጥቅም ሲገኝ በደካማ ጎናቸው በኩል ደግሞ በደል ይፈጸምብናል።

በዚህ ዓለም ላይ ፍጹም የሆነ ሰው ባለመኖሩ በግንኙነት ውስጥ ከደካማ ጎኑ የተነሣ በሌሎች ላይ በደል የማያደርስ ሰው አይኖርም። ይቅርታ ሰዎች ከደካማ ማንነታቸውና ባሕሪያቸው የተነሣ የሚፈጽሙትን በደል በመተው በምቹን ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ መቀበል ነው። ከተፈጸመ በደል ወይም በደሉ እንዲፈጸም ካደረገው የሰዎች ደካማ ጎን አልፎ ሰዎቹን መቀበል የሚያስችል ድርጊት ነው። ዴቪድ «ሌላውን ሰው እንዳለ ከልብ ከመቀበል ውጭ ይቅርታ ሊኖር አይችልም»[12] በማለት የተናገረው ቃል መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው አሳብ ነው። ይቅርታ የሚደረገው በደልን ለፈጸመው ሰው በመሆኑ በዳይን ሳይቀበል ይቅርታ ሊያደርግለት የሚችል ሰው አይኖርም።

በበብዓዊ እይታ ሲታይ ተበድሎ ይቅርታ ማድረግ አስቸጋሪ ነው። በተፈጥሮ የሚመጣው ምላሽ መበቀል ነው። ሰዎች ሳያውቁ ወይም ሆን ብለው አቅደውበት በእኛ ላይ በደል ሲፈጽሙ ይቅር ለማለት የሚያስችል መድኃኒት ፍቅር ነው። «ይቅርታ ቀላል ነገር የሚሆነው ዓለምን በፍቅር ዓይን በንመለከት ነው።»[13] ይህ ፍቅር በስሜት ግለት የተሞላ ሳይሆን በምንም ሁኔታ ውስጥ ሆኖ መልካም ነገርን ለማድረግ መሰጠት ያለበትን ውሳኔ ማድረግ ነው።

በዳይን መውደድ «ወርቅ ያለበትን ጭቃ መውደድ ሳይሆን በጭቃ ውስጥ ያለውን ወርቅ መውደድ» ነው። ወርቅን የማይወድ ሰው ባይኖርም ጭቃውን የሚጸየፍ ሰው ግን በጭቃ ውስጥ የተደበቀውን ወርቅ ለማግኘት ይቸገራል። የሚፈለገውና የሚወደደው ወርቅ የሚገኘው ከጭቃው ጋር በመነካካትና የማጽዳት ሂደትም ከተካሄደ በኋላ ነው። ለግንኙነቱ የሚፈለገው በዳዩ እንጂ በደሉ አይደለም። ተበዳይም የሚቀበለው በዳይን እንጂ በእርሱ ላይ የተፈጸመውን በደል አይደለም። በዚህ ሁኔታ ይቅርታ በሰብዓዊ ግንኙነት ውስጥ መበዳደል ቢኖርም ሰዎች እርስ በርሳቸው ተቀባብለውና ተዋድደው እንዲሁም ተቻችለው እንዲኖሩ መንገድ የሚከፍት በጎ ተግባር ይሆናል።

አጋፔ ፍቅር እንካ በአንካ ላይ ያልተመሠረተ በመሆኑ በከፉ ፈንታ መልካምን በማድረግ መርሕ የሚሠራ በስሆነ ለይቅርታ መሠረቱ ነው። «ይቅርታ የራሱን ሳይፈልግ ራሱን የሚሰጥ ነው። ጠላት ጥላቻን በሚጠብቅበት ሁኔታ ፍቅርን መስጠት ነው። ለጠላት ቅጣትና ፍርድ

---

[12] Augsburger, David. *The Freedom of Fogriveness*. P.37

[13] Jampolsky, G.G and et al. (1999) p. 5

ሲገባው ነፃነትን መስጠት ነው:: ጠላት ቁጣንና በቀልን ሲጠብቅ ጠላትን መረዳት መቻል ነው:: ይቅርታ የራሱን ጥቅም አይፈልግም:: ይቅርታ ለሌላው የራሱን ነፃነትንና ተስፋን ይሰጣል»[14]

### ይቅርታ በነጻ ፈቃድ ላይ የተመሠረተ በጎ ምላሽ ነው

ይቅርታ ማድረግ የፈቃድ ጉዳይ ነው:: በዳይን ይቅር ማለት የስውን ስሜትና ድርጊትን የሚያሳትፍ ሂደት ነው:: በሰው ተበድለን የሚሰማን ስሜት መጥፎ እንደሆነ የታወቀ ነው:: ስለዚያ ሰው ሰናስብ በውስጣችን የጥላቻና የቂም በቀል ስሜት ይሰማናል:: በውስጣችን የሚሰማንን ስሜት እምቢ ብሎን እየታገልን ለዚያ ሰው መልካም ነገር ማድረግ ስንጀምር በውስጣችን ያለው መጥፎ ስሜት እየቀነሰ ይመጣል:: መልካምና ትክክለኛ ስሜት ከመልካም ድርጊት በኋላ ተከትሎ የሚመጣ ክስተት ይሆናል:: በውስጣችን የሚሰማንን ስሜት እያዳመጥን ዕድሜ ልካችንን ለበደለን ሰው ይቅርታ ማድረግ አንችልም:: ከፉ ወይም በደል በእኛ ላይ ተፈጽሞ ጥሩ ስሜት ከተሰማን በኋላ ይቅርታ ለማድረግ ማሰብ የማይቻል ነገርን መጠበቅ ስለሆነ ኃላፊነት መዘንጋት እንዲሁም ፈውስና በረከታችንን ማዘግየት ይሆናል::

ይቅርታ ለማድረግ ፈቃዳችንን ከሰጠን ጥሩ ያልሆነው ስሜት እየተሰወጠ ይሄዳል:: የወሰንነውን መልካም ነገር እያደረግን ስንሄድ ስሜታችን ደግሞ እየተሰወጠ ይሄዳል:: ስሜት ድርጊታችንን ወይም የድርጊታችንን ውጤት በመከተል ይሰወጣል::

አንድ ክርስቲያን ጸሐፊ በቤተሰብ ውስጥ ባልና ሚስት ይቅርታ መደራረግ እንደሚገባቸው በሚያሳስብ መጽሐፋቸው ውስጥ ይቅርታን እንዲህ በማለት ገልጸታል:-

> ይቅርታ የፈቃድ ጉዳይ ነው፣ ሌላ ሰው በእኛ ላይ ያደረገውን ነገር ላለማሰላሰል ወይም ላለማውራት መወሰን ነው:: ይቅርታ በማወቅ የምናደርገው ምርጫና ሆን ብለን የምንወበደው ድርጊት ያለበት ሂደት ነው:: የትዳር ጓደኛ ተገቢ ባልሆነ ድርጊት ወይም ንግግር ላይ ያመጣውን ዕዳ መሰረዝ ነው:: የእግዚአብሔር ይቅርታ በእኛና በእርሱ መካከል ያቆምነውን የኃጢአታችንን ግድግዳ እንደሚሰብር ሁሉ የትዳር ጓደኞችንን ይቅር ማለትም በመካከላችን የተነቃቃ ኅብረት እንዲኖር መንገድ ይከፍታል:: ይቅርታ በበደል ምክንያት ተሰያይተን የነበርነውን ወገኖች እንደገና አንድ ላይ ያመጣናል::[15]

በዚህ አሳብ መሠረት ይቅርታ ሦስት ዋና ዋና አሳቦችን በውስጡ ያካተተ እንደሆነ እንመለከታለን:: የመጀመሪያው ይቅርታ በፈቃዳችን የምናደርገው ምርጫ መሆኑን ነው:: እውነተኛ ይቅርታ በነጻ ምርጫ የሚደረግ ውሳኔ ነው:: በራሳችን እውቀንና ፈቅደን ይቅርታ ስናደርግ ፍሬው ዘላቂነት ይኖረዋል:: ውሳኔው ከሚገለጥባቸው መንገዶች ሁለቱ ደግሞ የተፈጸመውን በደል ሁልጊዜ ላለማሰላሰልና ለሌሎች ሰዎች በወሬ ማስተላለፍን በመተው ይታወቃል::

ስለዚህ ይቅርታ ማድረግን መማር ከፈለግን ይቅር ለማለት ፈቃደኞች እንሁን:: ይቅርታ መስጠትና መቀበል የምንችለው ከተፈጸመብን በደል የተነሣ የተሰማንን መጥፎ ስሜቶችንና የደረሰብንን የሕይወት ቁስላችንን ለእግዚአብሔር ለመስጠት ፈቃደኛ በንሆን ነው:: እኛ ስምንይዛቸው እግዚአብሔር ቢይዛቸው የተሻለና ፈውስም እንደሚመጣ በማመን ለእርሱ መስጠት ነው:: ፈቃደኞች ሆነን የበደሉንን ሰዎች ይቅር ብንል መልካም የሆነ ፍሬን እንሰበስባለን፣ ባንፈቅድ ደግሞ ሕይወታችን ለስቃይ አሳልፈን ለመስጠት ወሰንን ማለት ነው:: ይቅርታ ማድረግና አለማድረግ የእኛ ምርጫ ነው:: ፈቃዱ ሲኖር መንገዱና ጸጋውም ይኖራል::

ሁለተኛው ይቅርታን ከዕዳ ስረዛ ጋር ማያያዙ ነው:: አንድ ሰው በሌሎች ላይ ተገቢ ያልሆነ ድርጊት ሲፈጽምና የማይገባውን ንግግር ሲናገር በራሱ ላይ ዕዳን ያስቀምጣል:: ምናልባት ያ ሰው እንዲህ ዓይነት ድርጊት እንዲፈጽም ወይም እንዲናገር ያደረጉት ውስጣዊና ውጫዊ ተጽዕኖዎች ሊኖሩ ይችላሉ:: በምንም ምክንያት ቢሆን አንድ ሰው ሌላውን ሲበድል በራሱ ላይ ዕዳን ያከማቻል:: በራሱ ላይ ዕዳን የቆለለውን ሰው ነጻ ለማውጣት ያለው አማራጭ ዕዳውን መሰረዝ ነው:: ያደጉ አገሮች ለደሃ አገሮች ያበደሩትን ዕዳ መክፈል ሲያቅታቸው እንዲሚሰርዙላቸው ዓይነት ማለት ነው:: ይህ የበደል ዕዳ የሚሰረዘው ደግሞ ለበዳዩ ምሕረት በማድረግ ነው::

በሰብዓዊ ግንኙነት ውስጥ በበዳይ የተፈጸመውን ዕዳ መሰረዝ የሚገለጽባቸው የተለያዩ መንገዶች አሉ:: አንድ ሰው የበዳይን የበደል ዕዳ መሰረዙን በሚከተሉት መንገዶች መግለጽ ይችላል:-

- ተከታታይነት ባለው ሁኔታ በደሉን ላለማሰብ በመወሰን
- የራስን በደል በማስታወስ
- ስለበደሉ በማሰብ መቆጣትን በመተው
- በዳይ ስለፈጸመው በደል እንዲቀጣ የሚፈልገውን እቅድን ለመተው በመወሰን
- በደሉን ለእግዚአብሔር አሳልፎ በመስጠትና በመሳሰሉት መንገዶች ይሆናል::

---

[14] David, A. P. 40

[15] Sande, K. (2002). *Peacemaking for Families: a biblical guide to managing conflict in your home*. Tyndale House Publishers, Inc., p. 85

በደሉ ወደሚመራህ ሳይሆን እግዚአብሔር ወዳቀደልህ መልካም ግብ ለመድረስ መሥራት ትችላለህ። በሕይወትህ ላይ የደረሰውን በደል እንደ መነሻ አድርገህ ከወለድከው ዓላማህ የበደሉህን ሰዎች መበቀል ወይም በደሉ በአንተ ላይ ያደረሰውን ውጤት ወይም ማንነት ይዘህ መኖር ነው። በደሉን በይቅርታ ብታልፈው ግን በሕይወትህ እግዚአብሔር መሆን የሚፈልገው ዓይነት ሰው የመሆን ዕድል አለህ። የአንተ ይቅርታ ያለፈውን ክስተት ባይለውጥም የወደፊት ሕይወትህን በበጎ ጎን ይለውጣል። ስለዚህ በአንተ ላይ የደረሰውን በደል በይቅርታ በመተው ዓላማህን ከግብ ለማድረስ ወደፊት ገስግስ። ወደፊት የሚጠብቅህ የሕይወት ሽልማት ማግኘት የምትችለው በሕይወትህ ላይ ለደረሰው በደል ተገዥ ሳትሆን ስትቀር ብቻ ነው። የበደሉህን ሰዎች ይቅር ብለህ በሕይወት ሩጫህ ፍጻሜ የምታገኘው ብድራት ጠላቶችህን ተበቅለህ አገኛለሁ ብለህ ከምትገምተው ብድራት እጅግ ይልቃል።

*ታደሰ የሚባል ወጣት ያደገው ከራሱ ጎሣ ውጭ በሆኑ ሰዎች መካከል ነበር። እርሱ ያደገበት ማሕበረሰብ ለእርሱ ጎሣ የነበረው አመለካከት ጥሩ አልነበረም። የታደሰ ጎሣ ከእነርሱ ያነሰና የተናቀ እንደሆነ እየነገሩት ይሰድቡትና ያንገላቱት ነበር። ብቻውንም ስለነበር አንዳንድ ጊዜ የአካል ጥቃትም ያደርሱበታል። በትምህርቱ ጎበዝ ተማሪ በመሆኑም ይቀኑበታል። በእርሱ በመበሳጫቸው በጣም በመናደዳቸው ስድብና አካላዊ ጥቃት በማድረስ ይበቀሉት ነበር። ታደሰ የልጅነት ዘመኑን ያሳለፈው በግዞት እንደሚኖር ዓይነት ሰው ነበር።*

*ወጣት ከሆነ በኋላ በእርሱ ላይ ይደረግ የነበሩትን ነገሮች ወደኋላ ሲመለከት «ለምን ነበር እንዲህ ያንገላቱኝ?» የሚል ጥያቄ መጠየቅ ጀመረ። በእርሱ ላይ በደረሰውም በደል ከማዘን አልፎ የቁጣ ስሜቱም እየጨመረ መጣ። ለትምህርቱ የሚሰጠውም ትኩረት እየቀነሰ ሄደ። አብዛኛውን ጊዜ የደረሰበትን በደልና በደለኞቹ ያሰላስላል። እንዴት አድርጎ በልጅነቱ ወቅት ያንገላቱት የነበሩትን በተለይም ማንነቱን ያንቋሸሹትን ሰዎች እንደሚበቀል አቀደ፤ ይህን ግን አንድ ቀን ለአንድ ሰው ማጫወት እንደሚገባው አሰበ። ዳሩ ግን ይህን ምስጢር ለማን ሊያካፍል እንደሚችል አላወቀም። በዚህ ሁኔታ በአሳብ እያለ የአባቱ ወዳጅ የነበሩት ሰው ትዝ አለው። አባቱ ከመሞቱ በፊት አንድ የልብ ወዳጅ ነበረው። ይህ ሰው አልፎ አልፎ አቤታቸው እየመጣ ለረጅም ጊዜ ከአባቱ ጋር ይጫወት ነበር።*

*ታደሰ የሁለተኛ ዓመት የኮሌጅ ትምህርቱን ጨርሶ ለእረፍት ወደ ሀገር ቤት ሊመለስ ወደ ሽማግሌው ሄዶ በልቡ ያለውን አሳብና ስሜት አካፈለው። ሽማግሌውም ታደሰ በልቡ ያለውን ነገር ለእርሱ በማካፈሉ የተሰማውን እርካታ ከገለጸ በኋላ ምን ዓይነት እርምጃ መውሰድ እንደሚገባው መከረው። «ሰዎች በተፈጥሮ እኩል መብት አላቸው። አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ወገኖች ከሌሎች እንደሚበልጡ ያስባሉ። እኛም በዚህ አካባቢ የተናቀ ወገን እንደሆንን እንቆጠራለን። እኛ የተናቅነው በሰዎቹ እይታ ነው እንጂ በብዙ ነገር ከእነርሱ የተሻለ ነገር አለን። ሙያችንም በጣም አስፈላጊ ነው። ሥራችን እንደ ሙያ የሚናቅ አይደለም። እነርሱም*



*ቢሆኑ ሙያችንን ይንቃሉ እንጂ የሙያችን ተጠቃሚዎች ናቸው። አንተም ብትሆን በትምህርትህ ከልጆቻቸው ትበልጣለህ። ብዙዎቹ የእነርሱ ልጆች ኮሌጅ አልገቡም። አንተ ግን አሁን ታታሪዎች የደረሱበት ሥፍራ ደርሰሃል።*

*«ስለዚህ ልጄ ሆይ! አሁንም የሚንቁን ሰዎች ለእኛ ሊሰጡን የሚፈልጉትን መጥፎ ስም ወደ ኋላ በመተው በትምህርትህ በርታ። እነርሱን ለመበቀል ብታስብ በእውነትም ከእነርሱ በታች ትሆናለህ። ይህን ጉዳይ ትተህ በትምህርትህ ብትበረታ ግን እኛ የምንናቅ ወገን እንዳይደለንና ከሚንቁንም ሰዎች ጋር እኩል እንደሆንን በተግባር ታሳያለህ። ከአንተም በኋላ ያሉ ልጆቻችን እንዲሁም የሚንቁን ሰዎች ልጆችም የአንተን ምሳሌነት በመከተል ሰው የደረሰበት ሥፍራ ይደርሳሉ» በማለት መልካም ምክር መከሩት። ታደሰም የኮሌጅ ትምህርቱን በከፍተኛ ውጤት በመጨረስ በኮሌጁ ውስጥ መምህር ሆነ። ከዚያም ትምህርቱን እስከ ዶክትሬት ድግሪ ድረስ በመማር በማስተማር ሙያው ቀጠለ። እርሱ ከተወለደበት ሥፍራ የመጡትን ብዙ ልጆችን አስተምሯል፤ ከጎሣውና ከሌላ የመጡትን የሠፈር ልጆች መካከል ልዩነት ሳያደርግ በሚያስፈልጋቸውም ነገር ይረዳቸዋል። የእርሱን ወገን የሚንቁም ሰዎች አፋቸውን ያዙ፤ ከታደሰ ጎሣም ጋር በመከባበር መኖር ጀመሩ።*

ታደሰ በልጅነት ወቅት ለዎች በእርሱ ላይ ያደርሱትን በደል በማሰብ እነርሱን የመበቀል እርምጃ ቢወስድ ኖሮ አሁን የደረሰበት ደረጃ ላይ አይደርስም ነበር። በዳዮቹን ለመበቀል ከማሰብ ይልቅ የወደፊት ሕይወቱን በገንቢ ሁኔታ በመለወጥ ላይ ትኩረት እንዲያደርግ በመመከሩና እርሱም ተመሳሳይ እርምጃ በመውሰዱ ሕይወቱን በቀና መንገድ መራው። በመልካምም ክፉውን ማሸነፍ እንደሚቻል አሳየ። በተወለደበትም አካባቢ በሚኖሩ የተለያዩ ጎሣዎች መካከል ዘላቂነት ያለው ተከባብሮ አብሮ መኖር የሚቻልበትን ሁኔታ ለመፍጠር ፈር-ቀዳጅ ሆነ።

የሕይወትን ሩጫ በትጋት ወደፊት ለመሮጥ ወደኋላ ማየት አሉታዊ ተጽዕኖ ያመጣል። ወደፊት የሚሮጥ ሰው ወደኋላ ሲመለከት የሩጫው ኃይልና ፍጥነት ይቀንሳል። በተገቢው ፍጥነትና ኃይል ወደፊት ለመሮጥ ለሩጫው እንቅፋት የሚሆኑትን ነገሮች ወደኋላ መተው አስፈላጊ ነው። ያለፈውን ጎጂ ክስተቶችን በአእምሮ ተሸክሞ የሕይወትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በትጋት መሮጥ አይቻልም። መጽሐፍ ቅዱስ «እኛ ደግሞ ሸክምን ሁሉ ቶሎም የሚከበንን ኃጢአት አስወግደን የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ» (ዕብ12:2) በማለት ይመክረናል።

ሩዋጮች ከባድ ሸክም ተሸክመው በተገቢው ሁኔታ መሮጥ አይችሉም። ሩጫና ሸክም አብረው የሚሄዱ ነገሮች አይደሉም። እግዚአብሐር ወዳቀደልህ ግብ እንዳትደርስ እንቅፋት ከሚሆኑብህ ነገሮች አንዱ ለበደሉ ሰዎች ይቅርታ አለማድረግ፤ ቂምና ምሬት ይዘህ ሁልጊዜ ስለ እነርሱ እያሰብክ መኖር ነው። በሌሎች ሰዎች ላይ ጥላቻ ወይም ቂም ካለህ ይህን ሸክም ዛሬውኑ ለማስወገድ እርምጃ መውሰድ ይኖርብሃል። ምናልባት

አንተን የበደሉ ሰዎች በሕይወት ላይኖሩ ይችላሉ:: አንተ ቂም የያዝክባቸውና ሸክም የሆኑብህ ሰዎች ምናልባት አንተንም ሳይሆን በታሪክ ውስጥ ወገንህን የበደሉ ሊሆኑ ይችላሉ:: ስለተፈጸመው በደል ከቤተሰቦችህ ሰምተህ ወይም ከታሪክ መጽሐፍ አንብበህ ይሆናል:: እነርሱ ሙታን ሆነው በመቃብር ሥፍራ ተኝተው በአንተ በሕያው በው፣ በምድር ላይ በምትንቀሳቀሰው ላይ ተጽዕኖ ያደርጋሉ:: ስለዚህ በሙታን አትሸነፍ:: ይቅር በላቸውና ጉዞህን ቀጥል::

የኋላ መስታወት እያዩ ወደፊት መንዳት እንደማይቻል ሁሉ ዛሬ ላይ ሆነህ በአእምሮህ ያለፈውን ሕይወት እያመነዠክህ የሕይወት ዓላማህን ከግብ ልታደርስ አትችልም:: ይቅርታ ማድረግ ባለፈው ዘመን የተፈጸመውን ስህተትና በደል ወደኋላ በመተው ያለ ሒሲና ክስ ወደፊት መገስገስ ያስችላል:: ይቅርታ የተሻለውን ነገር ለማድረግ በተስፋ መኖር ያስጀምራል:: አንድ የሥነመለኮት መምህር «ካለፈው የሕይወት መራርነት ነጻ አውጥቶን እጅግ አዲስ ወደሆነው ወደፊት ሊመራን የሚችለው ይቅርታ ማድረግ ብቻ ነው»[17] በማለት የተናገረው ጭብጥ ይቅርታ ማድረግ የሕይወት አቅጣጫ ለዋጭ መሆኑን ያስገነዝባል::

**ከሰዎች ጋር ባለህ ግንኙነት ሸክም ሆኖብህ ሕይወትህን ወደፊት በተገቢው ሁኔታ እንዳትመራህ ያደረገህ ነገር አለህን? በሰዎች ተበድለህ ቂም ይዘህ እየኖርክ ከሆንህ ይቅር በልና ወደፊት ተራመድ:: ቂም አንተን ካሰረበት እስር ቤት ውጣ:: የቂምና የይቅርታ አለማድረግ እስር ቤት ለማንም አልበጀም፣ ለአንተም አይበጅህም:: ለበደሉህ ሰዎች ይቅርታ ማድረግህ እነርሱ በአንተ ላይ የፈጸሙት በደል ይገባኛል ማለትህ አይደለም:: ከአንተ ይቅርታ ማድረግ የተነሣ እግዚአብሔርም በደላቸውን ይቅር ይላል ማለት አይደለም:: ለበዳዮች ይቅርታ ማድረግና መክልከል የእግዚአብሔር ጉዳይ ስለሆነ እርሱን ለእርሱ በመተው አንተ ማድረግ የሚገባህን መልካም ተግባር ፈጽም:: መለወጥ በማትችለው ባለፈው ነገር ከመታሰር የወደፊቱን ነገር ለመለወጥ ማድረግ የሚገባህን አንድ ነገር አድርግ:: እርሱም ይቅርታ ነው:: የበደሉህን ይቅር ማለት የሕይወትህ ፈውስ ጅማሬ ይሆናል::**

በዚህ ላይ አንድ ማስተዋል ያለብን መሠረታዊ አሳብ ይኖራል:: ለበደሉን ሰዎች ይቅርታ ማድረግና ከትናንቱ የሕይወት ገጠመኞቻችን ጋር ሰላምን መፍጠራችን በአንድ ጊዜ ከጨለማ ወደ ብርሃን እንደሚወጣ ዓይነት ሰው ሁለንተናዊ ሕይወታችንን ላይለውጥ ይችላል:: ይቅርታ ባለማድረጋችን የተያዙብን በረከቶቻችን ግን ይለቀቃሉ:: ሕይወታችን ሰላማዊ ይሆናል:: ሆኖም ሁልጊዜ በሂደት ውስጥ የምንመራቸውና የምንለማመዳቸው አዳዲስ

[17] Kruschw, R. B. (2001). *Christian Reflection: A Series in Faith and Ethics.* The Center of Christian Ethics. P. 5



ነገሮች ይኖራሉ:: ሕይወት ሂደት ስለሆነች ዛሬ ከሆነው ነገር ነገ ደግሞ ወደ ተሻለ ሕይወት ለመድረስ ተስፋ እናደርጋለን::

በግለሰብ ብቻም ሳይሆን እንደ ቡድን፣ ብሔረሰብና አገርም ስናስብ ላለፈው በደል ይቅርታ ማድረግ ለሰላም፣ ለብልጽግናና ለእውነተኛ አንድነት ቁልፍ ነው:: ከዛሬ ሁለት ወይም ሶስት መቶ ዓመታት በፊት የተደረገውን ታሪክ እየጠቀሱ ተበድለን ነበር እያሉ ተከታታይነት ባለው ሁኔታ ማውራት አንድ መልካም እርምጃን በማራመድ ገንቢ የሆነ ለውጥ ከማምጣት ይልቅ አሁን ያሉ ሰዎች/ሕዝቦች በሰላም አብረው እንዳይኖሩ በመካከላቸው ጥላቻንና ግጭትን መዝራት ነው::

ማጠቃለያ:

- ይቅርታ ከበደል የተነሣ የሚሰማንን መጥፎ ስሜት በመከተል የበቀል እርምጃ መውሰድን መተው ነው::
- በዳይ በፈጸመው በደል ተጸጽቶ ንስሐ በመግባት የጠፋውን ገንዘብ ወይም ንብረት መመለስን ላያስቀር ይችላል::
- የእግዚአብሔርን ምሕረት መለማመድ በሰብዓዊ ግንኙነት ውስጥ የሚፈጠረውን በደል በይቅርታ በማለፍ ከበዳይ ጋር የነበረውን ግንኙነት ለማደስ ዓይነተኛ መሣሪያ ነው::
- ይቅርታ ውስጣዊ ስሜታችንን በማዳመጥ የሚፈጸም ተግባራዊ እርምጃ ሳይሆን ፈቃድን በመጠቀም የሚወሰድ ውሳኔ ነው::
- ይቅርታ ያለፈውን መጥፎ የሕይወት ምዕራፍ በመዝጋት በአዲስ እይታ ወደፊት መጓዝ መጀመር ነው:: የራስን የነገ ሕይወት በበደል ላለመተርጎም ውሳኔ ማድረግ ነው::

የማሰላሰል ጥያቄዎች፡

(1) በዳይ ለፈጸመው በደል ካሣ መክፈል ምን ያህል መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት እንዲሁም ለግንኙነት መታደስ ምን ያህል ተጨባጭ ጥቅም ይኖረዋል?

(2) በወዳጅ መበደል በሩቅ በው ከመበደል የላቀ ሕመም የሚያስከትለው ለምንድነው? ወዳጅንስ ይቅር ማለት የሚከብደው ለምን ይሆን?

(3) በግለሰብ፣ በቡድን እንዲሁም በማሕበረሰብ ደረጃ በታሪክ ውስጥ የተፈጸሙትን በደሎች ወደኋላ በመተው በአዲስ እይታ ወደፊት መራመድ የሚቻለው ምን ዓይነት ተጨባጭ እርምጃዎችን በመውሰድ ይመስልሃል?

# 3
# ይቅርታ በዓውዳችን እይታ

በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል የተዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት ይቅርታን «ቂም ወይም ቅሬታ እንዳይኖር፡- በዳይ ተበዳይን ምህረት የሚጠይቅበት የልመና ቃል» እንዲሁም «በደልን፣ ቂምን ሙተው፣ ይቅር ማለት፣ ምህረት ማድረግ» በማለት ይተረጉመዋል።[18] በዚህ ትርጉም መሠረት በተበዳይና በበዳይ መካከል የሚፈጸም ክስተት ሆኖ በዳይ ተበዳይን ምህረት እንዲያደርግለት የሚጠይቅበት ሂደት ነው። በዳይ ተበዳይን ይቅርታ መጠየቅ የሚኖርበት ደግሞ በግንኙነታቸው ውስጥ ቂም ወይም ቅሬታ እንዳይኖር ለማድረግ ያለፈውን በደል በምህረት መተው ነው።

ስለ በደል፣ ቂምና ይቅርታ ከሚነገሩ የተለያዩ አባባሎች ማሕበረሰባችን ስለ ይቅርታ ያለውን ግንዛቤ መመልከት ይቻላል። ከዚህ በታች የተቀመጡት አሳቦች ግንዛቤ እንዲሰጡን ብቻ በማሰብ እንጂ ይቅርታ በተለያዩ ባሕሎች ውስጥ የተለያየ ትርጉምና ሂደት ሊኖረው እንደሚችል እስባለሁ። በዚህ አቅጣጫ ጥናቶች ቢደረጉ በዓውዳችን በይቅርታ ዙሪያ ለሚነሱ አሳቦች ሰፊ ግንዛቤ ማግኘት ይቻላል። ለጊዜው ይህን ማድረግ የዚህ መጽሐፍ ትኩረት በመሆኑ ለምሳሌ የሚሆኑ ጥቂቶችን ብቻ በማንሳት ማለፍ ግድ ይሆናል።

*በብዓዊ ፍጡር በደልን ይፈጽማል፡-* «ሰው ሆኖ የማይበድል፣ እንጨት ሆኖ የማይጨስ የለም» ማንኛውም ሰው በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ሌላውን ሰው ሊበድል ይችላል። ከሰው ልጅ ስህተት ስለማይጠፋ በዚህ ስህተት ደግሞ ሊጎዳ የሚችል ሰው መኖሩ የማይቀር ክስተት ነው። ስለዚህ በሰብዓዊ ግንኙነት ውስጥ በሰዎች በደል ሊፈጸም እንደሚችል ከወዲሁ ማሰብ ተገቢውን ቅድመ ዝግጅት ለማድረግ ይረዳል።

*ሰው መበደልን አይወድም፡-* «ሰው አይወድም በደል፣ በሬ አይወድም ገደል» በግንኙነት ውስጥ በደል እንደሚፈጸም ቢታወቅም ሰው በሌላው መበደልን አይፈልግም። ጤናማ አእምሮ ያለው ሰው ሌላው ሰው እንዲበድለው ሁኔታዎችን አያመቻችም። ተበድሎም መልካም ስሜት አይሰማውም። ይህ ሁኔታ ሰዎች በራሳቸው ላይ በደል እንዲደርስባቸው እንደማይወዱ ሁሉ ሌሎችንም ሳለመበደል ጥንቃቄ እንዲያደርጉ እንዲሁም የተበደለ ሰው መጥፎ ስሜት ሊሰማው እንደሚችል ያስረዳል። ተበዳይ የማይወደው ነገር ስለደረሰበት የሚሰጠውን አጸፋዊ ምላሽንም በትዕግሥት ለማስተናገድ ግንዛቤን ይሰጣል።

---

[18] እማርኛ መዝገበ ቃላት፡ 1993፡ ገጽ 167



*በው ለሚሠራው ክፉ ሥራ ብድራቱን ያገኛል፡-* «በሰፈሩት ቁና ሳይሠፈሩ አይቀሩም»፣ «ሰውን እንጎዳ ባይ እመድ ተንከባላይ» «ሥራ ለሠሪው፣ እሾህ ላጣሪው» ሰዎች በሌሎች ላይ የሚፈጽሙት ማንኛውም ተግባር አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ውጤት አለው። አንድ ሰው ሆን ብሎ ሌላውን ሰው ቢያጠቃ ወይም በሌላው ላይ ክፉ ሥራ ቢሠራና ቢጎዳው የኋላ ኋላ ተጎጂው ክፉ ድርጊትን የፈጸመው ሰው ነው። ሰውን ለመጉዳት ማሰብ ራስን ሳይጎዳ አይቀርም። ማንም ሰው ራሱን መጉዳት ስለማይፈልግ ሌላውን ሰው ከመጉዳት ሊቆጠብ ይገባል። ሌላውን ማጥቃት መልሶ መጠቃትን ወደ ራብ የሚመለስ ከሆነ ከሌላው ጋር በሰላም መኖር ይሻላል። «ሰው የዘራውን ያጭዳል» የሚለውን መንፈሳዊ መርሕ የሚያንጸባርቅ መልዕክት አለው። ክፉ ድርጊት ተፈጽሞ ክፉ ምላሽ የሚያስከትል ከሆነ ይህን በመተው ተቃራኒውን ማድረግ መልካም ብድራትን ያስገኛል ማለት ነው።

*ወሰንን መጠበቅ፡-* «ማርም ሲበዛ ይመራል» በሰብዓዊ ግንኙነት ውስጥ እያንዳንዱ ሰው ተገቢውን ወሰኑን በመጠበቅ አብሮ መኖር እንዳለበት የሚያሳስብ አባባል ነው። ከጅማሬ መልካም የሆነ ነገር ዘላቂነት ሊኖረው የሚችለው እያንዳንዱ ሰው የሌላውን መብትና ክብር እየጠበቀ ሲመላለስ ነው። እርስ በርስ መበዳደልና ይቅርታ መደራረግ ያለ ነገር ቢሆንም አንዱ ወገን ሌላውን ዝም ብሎ የሚበድል ከሆነ ግንኙነቱ ዘላቂነት አይኖረውም። ስለዚህ በግንኙነት ውስጥ ሰዎች የሚያገኙት ጥቅም ከሚደርስባቸው ጉዳት ካልበለጠ ግንኙነቱን ያፈርሱታል።

*በደል በንሰለት ለሰው፡-* «ሥጋ ቢወድቅ አፈር ይዞ ይነሳል» በሰብዓዊ ግንኙነት ውስጥ አንድ በደል በሚፈጠርበት ጊዜ ሌላ ችግር ደግሞ ከጎን ይወለዳል። በተቻለ መጠን በደል እንዳይፈጸም መከላከል ጥሩ ቢሆንም ከተፈጸመ በኋላ ግን መጀመሪያ ለተፈጠረው በደል ብቻም ሳይሆን በሂደት ለተወለዱ ችግሮችም ተገቢውን ምላሽ መስጠት ግንኙነቱን ለመፈወስ ይረዳል። በግንኙነት ውስጥ ያሉ ሰዎች መልካም እርምጃ ካልወሰዱ «ለእሳት ፍላት፣ ለጮማ ስባት» እንደሚባለው ነገሩ እየተባበሰ ይሄድና ግንኙነትን ከማፍረሱም በላይ በሁለቱም ወገኖች ላይ ያልታሰበ ኪሣራ ሊያደርስ ይችላል።

*ያለ ይቅርታ መንፈሳዊነት አይኖርም፡-* «ቂም ይዞ ጸሎት፣ ሳል ይዞ ስርቆት» «ሃይማኖት ክግብር፣ ጸሎት ከፍቅር» አንድ ሰው ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ አስቀድሞ ከሰብዓዊ ፍጡር ጋር ያለውን ግንኙነት ማስተካከል ይኖርበታል። በልብ ውስጥ ቂም እያለ ወደ አምላክ መቅረብ ለስሙ ጸሎት ማድረስ ቢባል ነው እንጂ ወደ እግዚአብሔር ደርሶ አዎንታዊ መልስ የሚያስገኝ ዓይነት ጸሎት አይሆንም። መንፈሳዊነት በልብ ንጽሕና ለናይ ምግባር በመፈጸም ይጀምራል። ጸሎት ከሰዎች ጋር በፍቅር በመኖር ኃይል ያገኛል።

*የበው ልብ በእግዚአብሔር ዘንድ ይታወቃል፡-* «ሰው ምን ቢዋሽ እግዜርን አያታልልም» እግዚአብሔር ሰው የሚናገረውን ቃል ብቻ ሳይሆን በልቡ ውስጥ ያለውን ትክክለኛ ነገርን ያውቃል:: ሰው በአንደበቱ ባልንጀራውን ሊያታልል ይችላል:: ነገር ግን እግዚአብሔር በሰው ንግግር ብልጠትና ስልት አይታለልም:: ስለዚህ በዎች በማጭበርበር የሰውን ኪሳ ማለፋቸው በአምላካቸውን ዘንድ በተመሳሳይ ሁኔታ ማለፍ እንደሚችሉ ማለብ የለባቸውም:: ሐሰት የሆነውን ነገር አምኖ መታለል የሰው እውቀት ውስንነት በመሆኑ አይኮነንም:: ነገሩ ግን ተናጋሪው አምላክ እንደሚጠይቀው ቢያውቅ ባልንጀሮቹን አያታልልም ነበር::

*ተቀናቃኝን በበጎ ጎን መመልከት፡-* «ምቀኛ አታሳጣኝ» አንድ ሰው ምቀኛ ካለው ጉዳት ሊደርስበት እንደሚችል በማሰብ ጥበብ በተሞላበት ሁኔታ ሕይወቱን ይመራል:: ምቀኛ ሌላውን ለመጉዳት አስበ የሚያደርጋቸው ነገሮች ለሌላው ሰው ጥቅም የሚሰጡ ሆነው ይገኛሉ::

ስለዚህ ይህ አባባል ሰው ምቀኛ ወይም ጠላት ቢኖረውም መልካም ነው የሚል አንድምታ አለው:: ይህ ማለት ግን በራስ ጥረት ጠላትን መፍጠር ተገቢ ነው ማለት ሳይሆን በግንኙነት ውስጥ ተቀናቃኝ ሰው በሚያጋጥምበት ጊዜ ያን ሰው ለግል ሕይወት ዕድገት ምክንያት አድርጎ ለመጠቀም መልካሙን ገጽታ ማየት የሚያስችል አእምሮ አስፈላጊ መሆኑን ለማስገንዘብ ነው::

*ይቅርታ መጠየቅና ምሕረት ማድረግ ያበ ነገር ነው፡-* «ሊበደሉ ማሩኝታ፣ ቢበደሉ ይቅርታ» በሰብዓዊ ግንኙነት ውስጥ አንዱ ሰው በሌላው ላይ በደል ሊፈጽም ስለሚችል ይቅርታ መጠየቅና ማድረግ የሚኖር ሂደት ነው። በዳይ ሊበድል ተበዳይን «እባክህን ማረኝ» ብሎ ሊጠይቀው እንደሚገባ ያሳስባል:: «ማረኝ» ብሎ መጠየቅ በሚኖርበት ዓውድ ደግሞ ተበዳይም በዳይን ይቅር ማለት ተገቢ መሆኑን ይናገራል:: በዚህ ምሕረት መጠየቅና ይቅርታ መስጠት ባለበት ግንኙነት ውስጥ ሰላማዊ የሆኑ ዘላቂ የሆነ ኅብረት ሊኖር ይችላል::

*ይቅርታ ከልብ ሊሆን ይገባል፡-* «ሲታጠቡ ከክንድ፣ ሊታረቁ ከሆድ» በግንኙነት ውስጥ በደል ሲፈጸም ሰዎች ይቅር ሊባባሉና እርቅን ሊፈጸሙ ይችላሉ:: አንዳንድ ጊዜ ይቅርታው ከላይ ላይ ብቻ ይሆንና ያለፈው ችግር እንደገና አገርሽቶ ግንኙነታቸውን ከፋኛ ይጎዳል:: ስለዚህ ሰዎች ይቅር ሲሉ ከልባቸው ማድረግ ይገባቸዋል:: ከልብ የሆነ ይቅርታ ለማድረግ ደግሞ ተገቢውን ሂደት መጨረስ አስፈላጊ ይሆናል::

*በደል ክብርን ይጎዳል፡-* «ጥቃት ከጥንብ ይገማል» በግንኙነት ውስጥ አንድ ሰው በደል ሲፈጸምበት የማንነት ክብር ጥቃትም ይደርስበታል:: ተበዳይ ለራሱ ያለው ክብር ወይም ለራሱ የሚኖረው ግለ-ምስል ይበላሻል:: በደል ውርደትን ያስከትላል:: ይህ ደግሞ በደል ከላይ የሚታየውን ጉዳት ብቻም ሳይሆን ውስጣዊ ማንነትን ስለሚጎዳ የይቅርታ



ሂደት ሲታሰብ በቀላሉ ለሚታየውም ሆነ ለማይታየው ለውስጣዊ ስብራት መፍትሔ መፈለግ አስፈላጊ መሆኑን ያሳስባል::

*በወዳጆች መካከል ያለው በደል ከፉ ነው፡-* «ጠላትህን የምትጠነቀቀው አንድ ጊዜ ነው፣ ወዳጅህን የምትጠነቀቀው ሁልጊዜ ነው» በግንኙነት ውስጥ ብዙ ጊዜ በደል የሚፈጸመው በጠላት ሳይሆን በወዳጅ ነው:: የጠበቀ ግንኙነት ያላቸው ሰዎች እርስ በርስ የመበዳደላቸው ሁኔታ የቅርብ ግንኙነት ከሌላቸው ሰዎች ይልቅ ይበልጣል:: ወዳጆች በቀላሉ እርስ በርስ መበዳደል ይችላሉ:: ምክንያቱም ወዳጆች *ሁልጊዜ* ስለሚገናኙ፣ ከግንኙነቱ መቀራረብ የተነሣ አንዱ ከሌላው የሚጠብቀው በጎ መነሳሳት ወይም አጸፋ ከፍተኛ በመሆኑ ትንሹም ነገር ጎልቶ ይታያል:: አንዳንድ ጊዜ ወዳጆች እርስ በርስ ከተበዳደሉ በኋላ ከልባቸው የሆነው ይቅርታ በመደራረግ አብረው እንዲኖሩ ለማድረግ ሊያስቸግር ይታያል:: ስለዚህ ከሩቅ ግንኙነት ይልቅ በጠበቀ ግንኙነት ውስጥ ለግንኙነት ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ያመለክታል::

*ካሣ መክፈል አስፈላጊ ነው፡-* «ለሚበት ያጎርሷል፣ ለተመታ ይክሷል» ያገባ ሰው ለሚበቱ ተገቢውን የፍቅር እንክብካቤ ማድረግ የሚጠበቅበት ተግባር ነው:: በተመሳሳይ ሁኔታ አንድ ሰው ሌላውን ከበደለ አስፈላጊውን ካሣ በመክፈል ጉዳቱን ማካካሱ ተገቢ እርምጃ ነው::

በዓውዳችን ውስጥ ከላይ የተጠቀሱት በሰብዓዊ ግንኙነት ውስጥ በደል ሲፈጸም በጎ የሆነ እርምጃ መውሰድን ማበረታታት ብቻም ሳይሆን ቂም ይዞ መበቀል፡ ክፉን በክፉ መመለስ የሚበረታታበትም ሁኔታ አልፎ አልፎ እንደሚታይ ማስተዋል ያስፈልጋል::

ማጠቃለያ፡

- አባባሎች በአንድ ማሕበረሰብ ውስጥ ሰዎች ስለ ይቅርታ-ሰብዓዊ ግንኙነት- ያላቸውን ግንዛቤዎችን፣ መመሪያዎችንና ምን መደረግ እንዳለበትና እንደሌለበት ይናገራሉ::
- በሰብዓዊ ግንኙነት ውስጥ የጠበቀ ግንኙነት ቢኖርም እርስ በርስ መበዳደል ሊኖር ይችላል:: ስለሆነም ይቅርታ መጠየቅና መስጠት አስፈላጊ መሆኑን ያስተምራል::
- በሰዎች መካከል የሚፈጸመው በደል ለበዳይ እንዲሁም ለተበዳይ የሚያመጣው ብድራት አለ:: ሆን ብሎ በሌሎች ሰዎች ላይ በደልን የሚፈጽም ሰው አሉታዊ ብድራት ማግኘቱ አይቀርም::
- የሰዎች በደል ከእግዚአብሔር ፊት የተሰወረ ነገር ባለመሆኑ ሰዎች የፈጸሙትን በደል መናዘዝ ያስፈልጋቸዋል::

**የማለላለል ጥያቄዎች:**

(1) በባሕላችሁ ውስጥ ስለ ይቅርታ የሚነገሩ ገንቢና አፍራሽ የሆኑ አባባሎችና ታሪኮችን ለመጥቀስ ሞክሩ:: እነዚህ አባባሎች ምን ያህል አስተሳሰባችሁን ቀርጸዋል ወይም በአስተሳሰባችሁ ላይ ያደረጉት አምንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖዎች ምንድናቸው?

(2) ከልጅነታችሁ ጀምራችሁ ስትሰሙአቸው ያደጋችሁት ታሪኮችና አባባሎች አሁን በሕይወታችሁ ላይ ምን ያህል ተጽዕኖ እንደሚያደርጉ አስተውላችሁ ታውቃላችሁን? ከምታስታውሱአቸው ነገሮች መካከል ጥቂት ምሳሌዎችን ለመስጠት ሞክሩ::

(3) በዓውዳችሁ ሰዎች ስለ ይቅርታ የሚያስቡአቸው አሳቦችንና አመለካከቶች ምን ያህል መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት አላቸው? ገንቢዎቹን ለመጠቀምና አሉታዊ ተጽዕኖ ያላቸውን ለመለወጥ ምን ማድረግ ይገባል?



# 4

# የይቅርታ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቶች

በአብዛኛው ይቅርታ ከሃይማኖት ትምህርት ጋር የተገናኘ አሳብ እንደሆነ ይታሰባል:: ከዚህም የተነሣ እንደ ሌሎቹ ትምህርቶች ሰፊ ሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር ሳይደረግበት ቆይቷል:: በእርግጥም ይቅርታ ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ መሠረት አለው:: በክርስትና እምነትም ይቅርታ እጅግ የላቀ ሥፍራ አለው:: በእግዚአብሔርና በሰው እንዲሁም በሰውና በሰው መካከል ባለው ግንኙነት ይቅርታ ያለው ሥፍራ ትልቅ ነው::

እምነት በዳይን ለማጥቃት ከሚያነሳሳቸው ማንኛውም አጸፋዊ ምላሽ ራሳቸውን መጠበቅ የሚያስችላቸውን አስተሳሰብ ይሰጣቸዋል:: ከዚህም በተጨማሪ እምነት ሰዎች ይቅርታ ለማድረግ በሚያስቡበት ወቅት ለሚያነሱአቸው እውነተኛ ፍትህን ማን ሊሰጥ ይችላል? ብሰው ለሚጠይቁት ጥያቄዎች መልስ በመስጠት ይቅር እንዲሉ ያግዛቸዋል:: ሰዎች በይቅርታ ሂደት ውስጥ በሚያልፉበት ወቅት ከመለኮት እገዛም በተጨማሪ ከማሕበረ-ምዕመናን የሚገኘውም ድጋፍ በያዙት አምንታዊ እርምጃ እንዲቀጥሉ ያበረታታቸዋል:: መጽሐፍ ቅዱስ ለሰዎች ይቅርታ እንድናደርግ የሚመክረንና የሚያዘንም ከዚሁ መሠረተ አሳብ በመነሳት ነው::

በዚህ ክፍል ይቅርታ ማድረግና መቀበል አስፈላጊ የሆነበትን ምክንያት የመጀመሪያውን- ከመንፈሳዊ እይታ እንመለከታለን:: መንፈሳዊ እይታውን መጽሐፍ ቅዱስ ይቅርታ ማድረግና መቀበል ያስፈልጋል ብሎ የሚያስተምርበትን ምክንያት እንዲሁም የሥነመለኮት ትምህርት ያላቸው የክርስቶስ ተከታዮች ከተረዱት እውነት በመነሣት ይቅርታ ስለ ማድረግ ያስተማሩትን ትምህርት ለመቃኘት እንሞክራለን:: ከእነዚህም የሚከተሱት የሚጠቀሱ ዋና ዋና ነጥቦች ናቸው:: እነርሱም:-

*የእግዚአብሔርን ምሳሌነት ለመከተል*

እግዚአብሔር በክርስቶስ የመስቀል ሥራ እኛን ኃጢአተኞችን ይቅር ስላለን እኛም ይቅርታን የተቀበልን ሰዎች ሌሎች ለሚበድሉን ሁሉ ይቅር ማለት ይገባናል;: ከዚህን አንጻር ስንመለከተው ይቅርታ የእግዚአብሔርን ዱካ መከተል የምንችልበት መንገድ፣ እግዚአብሔር ለሰዎች ያለውን እቅድ ተግባራዊ የምናደርግበት እንዲሁም ከእርሱ ጋር ያለንን ግንኙነት የምንጠብቅበትና የምናሳድግበትም መሣሪያ እንደሆነ ማየት እንችላለን:: ከእግዚአብሔር ይቅርታ እንደ ተቀበልን ለሌሎች ይቅርታ ለማድረግ ፈቃደኞች ካልሆንን በሕይወታችን የሚመጡ ብዙ ኪሣራዎች አሉ:: እነዚህን ነጥቦች ይቅርታ አለማድረግ የሚያስከትላቸው ነገሮች በሚለው ምዕራፍ ውስጥ በዝርዝር እንመለከታለን::

## ክርስቶስ በሕይወታችን ውስጥ እንደሚኖር ማስተዋል

ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛችንና ጌታችን አድርገን ከተቀበልን በኋላ እርሱ በሕይወታችን ውስጥ ይኖራል:: እርሱ በሕይወታችን ውስጥ እንዲገለጥ ከሚፈልጋቸው ባሕርያት መካከል አንዱ ፍቅር ነው:: ፍቅር ሲኖር ደግሞ ለሰዎች ይቅር ማለት ይኖራል:: ፍቅር ባለበት ሥፍራ ጥላቻና ምሬት አይኖርም:: በክርስቶስ በኩል የተገለጠው ፍጹም የሆነው የእግዚአብሔር ፍቅር እኛ እርሱ በተመላለሰበት መንገድ ስንመላለስ በሙላት ይገለጣል:: ክርስቶስ በሕይወታችን ውስጥ መኖሩን ስንረዳ በሰዎች ላይ ቂም መያዝና መጥላት አይገዛንም:: ለሰዎች ይቅርታ ማድረግ የሚያስችለንን ኃይል ከእርሱ እናገኛለን::

> ቃሉን ግን የሚጠብቅ ሁሉ በእርሱ የእግዚአብሔር ፍቅር በእውነት ተፈጽሞአል:: በእርሱ እንዳለን በዚህ እናውቃለን:: በእርሱ እኖራለሁ የሚል እርሱ እንደ ተመላለሰ ሁሉ ደግሞ ሊመላለስ ይገባዋል (1ዮሐ2:5-6)::

ቃሉን መታዘዛችን ክርስቶስ በእኛ ውስጥ እንዲኖር ያደርጋል:: እግዚአብሔር የሚኖረው እርሱን በሚታዘዙ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ነው:: ኢየሱስ ባስተማረው ትምህርት «የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፣ አባቴም ይወደዋል፣ ወደ እርሱም እንመጣለን፣ በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን» (ዮሐ14:23) በማለት ተናግሯል:: እርሱ በሕይወታችን ሲኖር ደግሞ ትዕዛዙን እንጠብቃለን:: በክርስቶስ ውስጥ መኖራችንና እርሱም በእኛ ሕይወት ውስጥ መኖሩ እውን መሆኑ የሚታወቀው እርሱ እንደ ተመላለሰ ስንመላለስ ነው:: እርሱ በብርሃን ይመላለስ ነበር:: ከሰዎች ጋር ባለው ግንኙነት የሰዎችን በደል ይቅር ይላል:: በምሕረቱ ብዙዎችን ወደ ራሱ ስብዋል:: እንዲህ ዓይነት ባሕርይ ካለው አምላክ ጋር የቅርብ ግንኙነት አለን የምንል ሰዎች በሰብዓዊ ግንኙነት ውስጥ የሚበድሉን ሰዎች ሲኖሩ ይቅርታ ማድረግ ከእርሱ ጋር ያለንን ኅብረት የሚገልጽ ዐቢይ ነጥብ ይሆናል::

## ለሰዎች ይቅርታ ማድረግ የክርስቲያናዊ ሕይወት ምልክት ነው

ሐዋርያው ጳውሎስ የእውነተኛ ክርስቲያን ሕይወት ምልክቶች እንደሆኑ ከዘረዘራቸው መሠረታዊ ነጥቦች መካከል አንዱ ለሰዎች ይቅርታ ማድረግ ነው (ሮሜ12:17-21):: በዚህ አሳብ ውስጥ የተጠቃለሉ ብዙ ንዑሳን አሳቦችንም እናገኛለን:: ይቅርታ ማድረግ ለማንም ሰው ስለ ክፉ ፈንታ ክፉን አለመመለስ፣ በሰዎች ዘንድ በጎ የሆነውን ማሰብ፣ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ለመኖር በእኛ በኩል ማድረግ የሚገባንን መልካም ነገር ሁሉ ማድረግ፣ በራሳችን ከመበቀል ይልቅ በቀልን ለእግዚአብሔር መተው፣ ለጠላት መልካም ነገር በማድረግ በጎ የሆነ አእምሮ እንዲኖረው መርዳትና ክፉውን በመልካም ለማሸነፍ መወሰን ናቸው::

ሰዎችን ይቅር ማለት የክርስቲያናዊ ሥነምግባር መገለጫ ነው:: ለክርስቶስ ተከታዮች ለበዳይ ይቅርታ ማድረግ የእግዚአብሔርን ፍቅርና



ይቅር ባይነት ባሕርይንና እርሱ ለሰው ልጅ ያለውን በሁኔታዎች ላይ ያልተመሠረተ ተቀባይነት ነጸብራቅ ነው:: በሌሎች ሰዎች ተበድለው እነርሱን ይቅር ማለት መቻል በእኛ ውስጥ የመለኮት ባሕርይ እየተገለጠ እንደሆነ ማሳየታችን ነው:: ከዚህ አንጻር ስንመለከተው ይቅርታ ማድረግና አለማድረግ እኛ ስለ እግዚአብሔር ያለንን አምነት/አስተሳሰብና እርሱ ለሰው ልጆች ያለውን ዓላማ የምንረዳበትን ሁኔታ የሚገልጽ ነው::

የክርስቶስ ተከታዮች በሰዎች ተበድለው ይቅርታ ለማድረግ ፈቃደኛ አለመሆናቸው እነርሱ የሚያመልኩት አምላክ በሰው ልጆች ላይ ቂም የሚይዝ አምላክ እንደሆነ አድርገው ያሳያሉ:: የእግዚአብሔር ባሕርይና ማንነቱ በሰዎች አስተሳሰብና ድርጊት ላይ ባይመሠረትም የክርስቲያኖች ይቅርታ አለማድረግ እግዚአብሔር ይቅርታ የማያደርግ አምልክ መሆኑን ያመለክታል:: በተቃራኒው ደግሞ ተበድሎ ይቅርታ ማድረግ የእግዚአብሔርን ይቅር ባይነትን ያሳያል::

በክርስቶስ የሆኑ ሰዎች አንዱ መሠረታዊ መገለጫቸው እርስ በርስ ይቅር መባባላቸው ነው:: በክርስቶስ ይቅር ስለተባሉ አንዱ ለሌላው ይቅርታን መስጠትና መቀበል ባሕርያቸው ነው (ኤፌ4:32):: እርስ በርስ ይቅር እንዲባባሉ ምክንያት የሆነውም ስለ ሌሎች ያላቸው በጎ አመለካከትና ርኅራኄ ነው:: ከእግዚአብሔር የተቀበሉትን ነገር ለሌሎች ለመስጠት አይነፍጉም:: በክርስቶስ ኢየሱስ መስዋዕትነት የተገኘውንና የተቀበሉትን ይቅርታ በርኅራኄ መንፈስ ተነድተው ለሌሎች ሰዎች ያካፍላሉ:: ሰዎች የእግዚአብሔርን ይቅርታ ለማግኘት ከልጁ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በግል መተዋወቅ ያስፈልጋቸዋል::

በእውነተኛ ንስሐ ያገኙትን ይቅርታ በሕይወታቸው ተለማምደው በተመሳሳይ ሁኔታ እንደ እነርሱ ኃጢአተኞች ለሆኑት ደግሞ በግንኙነት ውስጥ በደል ሲደርስባቸው ይቅርታ ለማድረግ ለሰዎች ቸርነትና ርኅራኄ ያላቸው ሰዎች ሊሆኑ ይገባቸዋል:: ለሰዎች ቸርነትና ርኅራኄ የሌላቸው ወገኖች ለሌሎች ይቅርታ ማድረግ አይሆንላቸውም:: ሌሎችን ይቅር ለማለት የሚያስችለው የመንፈስ ፍሬ በሕይወት ውስጥ ሞልቶ መኖር ነው:: በዚህም ይቅርታ ማድረግ የመንፈሳዊ ፍሬ ውጤት እንደሆነ እንመለከታለን::

*በዳይ ባደረሰው በደል መሰቃየቱን አለመፈለግ*

እንዳንድ ጊዜ በዳይ በእኛ ላይ በፈጸመው በደል በሰላምና በእርጋት የሚኖር ሊመስለን ይችላል። እልፎ አልፎ በሰዎች ላይ ባደረሱት በደል የሕሊና ጸጸት የማይሰማቸውና በፈጸሙት በደል የሚደሰቱ የስብእና ችግር ያላቸው ሰዎች መኖራቸው ባይካድም በአብዛኛው ሰዎች በሌሎች ላይ በማወቅ በደል ፈጽመው በሰላም አይኖሩም። ከውጭ የሚናገራቸው አካል ባይኖርም ማንንም የማይፈራው በውስጣቸው ያለው ዳኛ ሳያቋርጥ ይፈርድባቸዋል። ከዚህም የሕሊና ክስ የተነሣ ተበዳይ የሰላም መንገድ እንዲከፍትላቸው ይሻሉ። ተበዳይ ራሱን በበዳይ ሥፍራ በማስቀመጥ ሁኔታውን መረዳት ከቻለ ይቅርታ ለማድረግ ፈቃደኛ ይሆናል። እንደ እኛው ያለው ሰው ሰላምና እረፍት በማጣት እንዲጨነቅ አለመፈለግ ወደ ይቅርታ ያመራል።

በዳይን ከሕሊና ክስ ነጻ ለማውጣት ቁልፍ ያለው ሰው ቢኖር ተበዳይ ነው። በዳይ በእኛ ላይ በፈጸመው በደል በሕሊና ክስ እየተሰቃየ እያለ እኛ ዝም ብለን እንዲሰቃይ ማድረጉ ተገቢ ነውን? በዚህ ዓይነት ሁኔታ ተበዳይ ከበዳይ የተሻለ ያደረገው ነገር አለ ወይ? ተበዳይም በተራው በዳይ መሆኑ አይደለም ወይ?

*አማኑኤል በቤተክርስቲያን ከአንዲት ቆንጆ ሴት ልጅ ይተዋወቅና በጓደኝነት ለጥቂት ዓመታት አብረው እንደ ቆዩ ለትዳር ይጠይቃታል። እርስዋ ፈቃደኛ እንደሆነችና የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑንም መረዳት እንዳገኘች ገለጸችለት። ሁለቱም አንድ ላይ ሆነው ውሳኔያቸውን ለቤተክርስቲያን መጋቢ አሳወቁ። በአጭኝነት እንዳሉ ከአማኑኤል የተሻለ የኢኮኖሚ አቋም ያለው ጎልማሳ ለትዳር ጥያቄ ያቀርብላታል። እርስዋም ምንም ሳታመነታ አማኑኤልን ወደ ኋላ ትታ ከሰውየው ጋር ግንኙነት ጀመረች። ከአማኑኤልም እየሸሸች መጣች። በመጨረሻም እርሱን እንደማትፈልገውና ግንኙነታቸውም የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዳልሆነ በመግለጽ የትዳር ምርጫዋን ከአዲሱ ሰው ጋር አደረገች።*

*የአማኑኤል ሕይወት እንደ ሸክላ ዕቃ ተሰባበረ። ለሕይወት ያለው ተስፋ ጨለመበት። ሐዘንና የመንፈስ መውደቅ ደረሰበት። ለሥራው እንዲሁም ለመንፈሳዊ አገልግሎት የነበረው የልብ መነሳሳት ከዳው። ጓደኞቹም ሸሹት። አልፎ አልፎ እንጂ አምልኮ መሄድንም አቆመ። ስለእንግዲህ ሰውን ማመን ከቶም አይቻልም በሚል ውሳኔ ላይ ደረሰ። እርሱ በዚህ ሁኔታ ሲሰቃይ የቀድሞ እጮኛው ግን በዚያው ቤተክርስቲያን አገባች። አማኑኤል እርስዋን እንደገና ማግኘት እንደማይችል ሲረዳ ራሱን ለማረጋጋት ወሰነ። ከአንድ የወጣት አማካሪ ጋር በነበረው ግንኙነት ሕይወቱን በመልካም ሁኔታ ለመምራት የሚያስችለውን አቅም እያሳደገ መጣ። የቀድሞ መንፈሳዊ መነቃቃትንና በሥራ ላይ ያለው ትጋት ተመለሰለት። እንደ ቀድሞ ደስተኛ መሆን ቻለ። ሆኖም ለእጮኛው ያለው አሳብ ጥሩ አይደለም። መቼም እኔን እንደ እርሜ ጫማ ጥላኝ ሄዳ ሕይወትዋ መልካም አይሆንላትም እያለ ያስባል። እግዚአብሔር የእጅዋን ሥራ እንደሚሰጣትም ይጠብቃል።*



*የቀድሞ እጮኛው በትዳርዋ የጎደላት ነገር ባይኖርም በአማኑኤል ላይ ያደረገችው ነገር ትክክል እንዳልነበረ ማስተዋል ጀመረች። እንደ እማኝ ማድረግ የማይገባትን ነገር እንዳደረገችበት ተገነዘበች። የትዳር ውሳኔና ምርጫው የራስዋ እንደሆነ ብታስብም እርምጃውን የወሰደችበት ሂደት ግን ክርስቲያናዊ ሥነምግባርን የጠበቀ እንዳልሆነ በመገንዘብዋ ልብዋ ማዘን ጀመረ። በዚህም አማኑኤልን ይቅርታ መጠየቅ ለሕይወትዋ ደስታዋን እንደሚመልስላት አሰበች። እርሱን ለመቅረብና ሰላም ለማለት በምትሞክርበት ጊዜ አማኑኤል ፊት አይሰጣትም። እርስዋ ስትቀርበው እርሱ ደግሞ ሲርቃት ልቡ በሆነው ነገር በመጎዳቱ ነው ብላ እያሰበች ከፊት ይልቅ እየተጎዳች ሄደች። ከእርሱ ጋር ለመነጋገር የምታደርገው ጥረት በተከታታይ ሳይሳካ ስለቀረ ከፊት ይልቅ ሐዘንዋ ጨመረ። በትዳር ሕይወትዋም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አመጣ።*

*አንድ ቀን አማኑኤል ሲጸልይ በዓይነ ሕሊናው ለለምለም ሣር መሐል ባለው ደረቅ መሬት ላይ የታሰረች አንዲት በግን ያያል። በውስጡ ደግሞ «ይህችን በግ ፍታትና ሣሩን ትብላ» የሚል መልዕክትን ይሰማል። በጣም ግራ ገባው። እንደ ምንም ብሎ ጸሎቱን ጨርሶ ተነሣ። ያየው ነገርና የሰማው መልዕክት ከአእምሮው አልጠፋም። አንድ ቀን ሲመሽ አየር ለመናፈስ በመንገድ ላይ እየተራመደ እያለ አንተ ያሰርካት በግ የቀድሞ እጮኛህ ናት የሚል ድምጽ ከውስጡ ደወለ። አማኑኤል የሰማውን ነገር ማመን አቃተው። ወደ ቤቱ ተመልሶ በእግዚአብሔር ፊት ተንበርክኮ «ጌታ ሆይ! ይቅር በለኝ! ለእርስዋ ከልቤ ይቅርታ የማደርግበትን ጸጋ ስጠኝ» ብሎ ለመነ። ከእርስዋ ጋር ሳይገኛኝ እግዚአብሔር ሕይወትዋንና ትዳርዋን እንዲባርክላት በመጸለይ ጀመረ።*

*እንደ ለመደችው ከአምልኮ በኋላ ሰላም ለማለት ወደ እርሱ ስትቀርብ ፈገግ ብሎ ሰላም አላት። እንባዋ በዓይኖቹዋ ሞልተው «አባክህን ይቅር በለኝ» አለችው። አማኑኤልም አቀፋትና «ከልቤ ይቅር ብየሻለሁ» አላት። አብረው ለጥቂት ጊዜ ከተነጋገሩ በኋላ ሁለቱም በደስታ ተሞሉ። አሁን በቤተክርስቲያን ውስጥ እንደ ክርስቲያን ወንድምና እህት ይተያያሉ።*

ሰዎች በደል ፈጽመው በሰላም ይኖራሉ ማለት አይቻልም። በመጀመሪያ እንኳ ባደረጉት በደል በተበዳይ ላይ የደረሰውን ጉዳት መመልከት ባይችሉ በጊዜ ሂደት ሕሊናቸው እየወቀሳቸው ይሄዳል። በዚህ ጊዜ ወደ ተበዳይ ለመቅረብና ሁኔታውን ለማስተካከል የሚያደርጉት ጥረት ሲከሽፍባቸው ስቃያቸው ይጨምራል፤ ሁለንተናዊ ሕይወታቸው ይናጋል። በበዳይ ሕይወት ውስጥ እንዲህ ዓይነት ሁኔታ መፈጠሩን ተበዳይ እያውቅም፣ እንዲህ ይሆናል ብሎም ለማሰብ ይቸገራል። ተበዳይ የራሱንም ሆነ የበዳይን ሕይወት ለመፍታት ለበዳይ መልካምን ሕይወት መመኘት ወደሚያስችለው ደረጃ ለመምጣት በውስጡ መንፈሳዊ ተሐድሶ ያስፈልጋል። በዳይ ሁኔታውን ለማስተካከል የሚወስዳቸውን እርምጃዎች በበጎ ሕሊና በመመልከት ለመተባበር ፈቃደኛ መሆን ሁለቱንም የሚያረካ ውጤት እንዲገኝ ምክንያት ይሆናል።

*ሰዎችን በልብ መጥላትና ቂም መያዝ ኃጢአት በመሆኑ*

ይቅርታ በሰዎች ላይ ቂም አለመያዝና ስመበቀል እርምጃ ከመውሰድ መቆጠብ ነው። አንድ ሰው በእኛ ላይ ባደረገው በደል በመቆጣት ቂም ይዞ ለተፈጸመው በደል ለበቀል መነሳት ከአንድ የክርስቶስ ተከታይ የሚጠበቅ እርምጃ አይደለም። ለምን? መጽሐፍ ቅዱስ ቂም ይዞ ስበቀል መነሳት ትክክለኛ እርምጃ እንዳልሆነ ያስተምራል።

> «ወንድምህን በልብህ አትጥላው፣ በባልንጀራህ ምክንያት ኃጢአት እንዳይሆንብህ ገሥጸው። አትበቀልም፣ በሕዝብህም ልጆች ቂም አትያዝ፣ ነገር ግን ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ፣ እኔ እግዚአብሔር ነኝ» (ዘሌ19:18)

የበደሉንን ሰዎች በልባችን መጥላት እንችላለን። ሰዎች በልባችን ውስጥ ያለውን ነገር ማየት ስለማይችሉ በውስጣችን እየጠላናቸው ከእነርሱ ጋር ግብዝነት ያለበት ግንኙነት እናደርጋለን። ከእነርሱ ጋር በጥሩ መንፈስ እንዳለን እናስመስላለን። ነገር ግን በልባችን ውስጥ ያለው ጥላቻ ከሰዎች የተሰወረ ነገር ቢሆንም እግዚአብሔር ግን ይመለከተዋል። በልባችን ውስጥ ያለው አሳብና ስሜት በሕያው እግዚአብሔር ፊት የተገለጠ ነው። ...

በልባችን ውስጥ ያለው ጥላቻ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት ነው። ከልባችን ጥላቻን ማስወገድ ያለብን ሰዎች ስለሚያዩት ወይም ይታወቅብናል ብለን ፈርተን ሳይሆን ሳይገለጥ ቢቀመጥም ኃጢአት ስለሆነ ነው። በልባችን ያለው ጥላቻ ሰዎች ባያውቁትም በሕይወታችን እግዚአብሔር ወዳቀደልን መልካም ግብ እንዳንደርስ እንቅፋት ይሆንብናል።

ስልባችን ከጠላን ሰው ጋር መልካም ግንኙነት ሊኖረን አይችልም። የልብ ጥላቻ ስግንኙነት ውስጥ ትልቅ ግድግዳ ይሆናል። ሰዎች ፊት ለፊት በአካል እንዳይተያዩ፣ እርስ በርሳቸው እንዳይነጋገሩ፣ ሰላምታ እንዳይጠያየቁና እንዲከራረፉ ያደርጋል።

የመልካም ግንኙነት ጠላት የሆነው በደልን መቁጠርና ቂም መያዝ መፍትሔው ይቅር መባባል ነው። በአብዛኛው የብዙዎችን መልካም ግንኙነት ያፈረሰው ጠላት ይቅርታ አስማድረግ ነው። አማኞች በኅብረት ውስጥ በሚኖሩበት ወቅት በመካከላቸው በደል ሊፈጸም ይችላል። ይህ እንግዳ ነገር አይደለም። ምክንያቱም እጅግ በጣም በሚዋደዱ ወዳጆች መካከል ግጭት እንዳይፈጠር መከልከል ክቶም አይቻልም። ነገር ግን በደል ሲኖር በደሉን በጸጋ መያዝን መማር የነበረውን ግንኙነት እንዳይበላሽ ያደርጋል። ማንም ምዕመን በኅብረቱ ውስጥ ባለው ወንድም ወይም እህት ላይ የሚነቀፈው ነገር ካለው በመነጋገር ይቅርታ መደራረግ እየተቻለ በጥላቻና በቂም ስሜት አብረው መኖር ከክርስቲያናዊ ሥነምግባር የራቀ ሕይወት ነው።

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች በውጭ ባላቸው ሁኔታ «ሰላማዊ» መስለው አብረው እየኖሩ በልባቸው ውስጥ ግን ለግድያ የሚፈላለጉ ዓይነት ሊሆኑ ይችላሉ። በጸሎታቸው እንኳ ሳይቀር በልባቸው ውስጥ ያለውን ስሜት



ሊያንጸባርቁ ይችላሉ። «ጠላት» ብለው ሊቃወሙ ሰይጣንን ሳይሆን በልባቸው የጠሉትን ሰው ሊያመለክቱ ይችላሉ። ሰው ከውጭ ያለውን ነገር ያያል እንዲሁም ይሰማል፣ እግዚአብሔር ግን የልብን ዓላማ ይመዝናል። እጅግ የከበረ ዋጋ ያለው በአንደበታችን የሚወጣው ሳይሆን የልባችን ቅንነትና ንጽሕና ነው።

*በቀልን ለእግዚአብሔር መተውና ለበዳይ መልካም ማድረግ ዘላቂ ሰላም ስለሚያመጣ*

እግዚአብሔር «በቀል የእኔ ነው እኔ ብድራቱን እመልሳለሁ» (ሮሜ12:19) በማለት ተናግሯል። በአንዳንድ ሁኔታዎች ከሰዎች ጋር ሰላምን መፍጠር የማይቻልበት ሁኔታ ሊያጋጥም ይችላል። በግንኙነት ውስጥ አለመግባባትና ግጭት በሚፈጠርበት ወቅት ግጭቱን ለመፍታት ኃላፊነት መውሰድ አስፈላጊ ነው። የክርስቶስ ተከታዮች ሌላው ወገን ሰላምን እንዲፈጥር ጫና ማሳደር የሚችሉበት ሁኔታ ላይገጥማቸው ይችል ይሆናል። ሌላውን ወደ ሰላማዊ ውይይት ማምጣት ባይችሉም እንኳ የተከሰተው አለመግባባት ወደ ከፋ ግጭት እንዳያመራና ግንኙነቱ እንዳይቋረጥ በራሳቸው በኩል ሰላማዊ የሆነ እርምጃ መውሰድ ይገባቸዋል። እግዚአብሔር በዚህ ዓለም እንድንኖር የፈቀደው ሰላምን እንድናመጣ እንጂ በሰዎች ግንኙነት መካከል መለያየትና መከፋፈልን እንድናመጣ አይደለም።

በእኛ በኩል ከሰዎች ሁሉ ጋር በሰላም ለመኖር የሰላምን መርሕና እርምጃ መከተል ዋጋ ሊያስከፍል የሚችል እንደሆነ ከወዲሁ ማወቅ ያስፈልጋል። አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ሰዎች የክርስቶስ ተከታዮች አይበቀሉንም ብለው የሰላሙን እርምጃ ለራሳቸው ጥቅም ለመጠቀም ኢፍትሐዊ ድርጊት ያሳያሉ። ሰዎች የሰላምን መንገድ ለማጨናገፍ ምንም ዓይነት እርምጃ ቢወስዱ የክርስቶስ ተከታዮች የሰላምን መርሕና እርምጃ መልቀቅ የለባቸውም። ምክንያቱም የእምነታችን መሪ ይህን መንገድ በመከተል ትክክለኛውን ጎዳና ያሳየን በመሆኑ ነው። የእርሱ ተከታዮች ነን ካልን የእርሱን ዱካ መከተል ስምርጫ ውስጥ የሚገባ ጉዳይ አይደለም።

> እንደ ክርስቶስ ተከታዮች ሰዎች በእኛ ላይ ክፉ ነገር በሚሠሩበት ጊዜ በራሳችን ሰዎቹ ስለፈጸሙብን በደል ብድራት መመለስ የማይገባን በቀል ስላልተፈቀደልን ነው። ሰዎች ስፈጸሙት በደል ጻድቅ ፈራጅ ዳኛ እግዚአብሔር ነው እንጂ እኛ አይደለንም። እኛን በሰዎች ላይ ዳኛ አድርጎ ማንም አልሾመንም። ሰዎች ሲበድሉን እነርሱን ለመበቀል መነሣት ግን በራሳችን በሰዎች ላይ ዳኛ አድርገን መሾም ነው። ይህ ደግሞ የእግዚአብሔርን የፍርድ ወንበር መቀማት ነው። የእርሱን ኃላፊነት በራሳችን መውሰድ ነው። ይህ ሁኔታ ደግሞ ከሰዎች ጋር ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ሥልጣንም ጋር እንድንጋጭ ያደርገናል።

ይቅርታ ማድረግ ከሥጋዊና ዓለማዊ እይታ የተለየ ተግባር ነው:: ጠላትን ወይም በዳይን ይቅር ማለት የዓለም እሴት አይደለም:: ይቅርታ የበቀልን ስሜት ለማጥፋትና በግንኙነት ውስጥ እውነተኛ እርቅ ለማምጣት ዓይነተኛ መሣሪያ ነው:: ይቅርታ ሰዎች በሌሎች ላይ ያሰቡትን ክፉ ነገር እንዳያደርጉ ይመልሳቸዋል:: ጠላት ወይም በዳይ የተደረገለትን ይቅርታ በሚያይበት ጊዜ ወደፊት በዚያ ተግባር እንዳይቀጥል ያደርገዋል:: «እኔ እንዲህ ያለ በደል ፈጽሜ እያለሁ እንዴት ይቅር ሊለኝ ቻለ?» የሚለውን ጥያቄ ይጠይቃል:: ያልተጠበቀ መልካም ነገር ሲደረግለት ወደ አእምሮው ይመለስና ያደረገውን ነገር ለማስላሰል ዕድል ያገኛል:: በዚህ መንገድ ይቅርታ የበደልን ቀጣይነት ያጠፋል::

*ይቅርታ ማድረግ ጠላትን ወዳጅ የማድረጊያ መንገድ በመሆኑ*

ማንኛውም ጤናማ አመለካከት ያለው ሰው ጠላት እንዲኖረው አይሻም:: በሕይወት ውስጥ ጠላት ቢገጥመውም ማጥፋትን ይፈልጋል:: ሰዎች ተበድለው ሳሉ በዳዮቻቸውን ቢበቀሉ እንደሚያጠፉአቸው ያስባሉ:: ነገር ግን በቀል ጠላትን የማጥፊያ ጥሩ ዘዴ አይደለም:: ጠላትን ለማጥፋት እጅግ የተዋጣለት ስኬታማ መሣሪያ ጠላትህን ወዳጅ ማድረግ ነው:: በመልካም ታሪኩ ብዙዎች የሚያስታውሱት አብርሃም ሊንከን የተባለው የቀድሞ የአሜሪካን ፕሬዘዳንት «ጠላቶቼን የማጠፋቸው ወዳጆቼ ሳደርጋቸው ነው» ብሎ ተናግሮ ነበር:: በቀል ጠላትን ያበዛል! ወዳጅ ማድረግ ግን ጠላትን ያጠፋል::

የክርስቶስ ተከታዮች መበቀል የማይገባቸው ሌላው ምክንያት ደግሞ ሰዎች ክፉ ከሠሩ ክፉውን መመለስ ሰዎች መልካም ባሕርይ እንዲማሩ የማድረግ እቅም ስለ ማይኖረው ነው:: ሰዎች ክፉ ነገር ሲያደርጉ በቸርነት በጎ ነገርን ማሳየት ወደ መልካም ነገር ይመራቸዋል:: በቀል ክፉ አሳብና ድርጊት ቀጣይነት እንዲኖረው ሲያደርግ መልካም ነገርን ማድረግ ደግሞ የክፉ አሳብና ድርጊትን ምንጭ ያደርቃል:: ከዚህ ዓለም ክፉ ድርጊት እንዲጠፋ ለማድረግ በደል ሲፈጸም እያንዳንዱ ሰው በመልካም ሁኔታ ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል::

ክፉ የፈጸሙትን ሰዎች መበቀል በክፉ መሸነፍ ነው:: በማንኛውም ግንኙነት ውስጥ ክፉን በክፉ ማሸነፍ አይቻልም:: ክፉ ነገር የሚሸነፍበት ዋነኛው መንገድ ክፉ ብድራት በመስጠት ሳይሆን መልካም ነገር በመሥራት ነው:: ክፉ ድርጊትን የማሸነፍ ኃይል ያለው መልካም ድርጊት ነው:: ሰዎች ከጠላትነት ከልል ወደ ጓደኝነት መሥመር ውስጥ የሚገቡት በመልካም ሥራ ነው:: እነርሱ ክፉ ሲያደርጉ መልካም በመሥራት ዳግመኛ በእኛ ላይ ክፉ እንዳይሠሩ ማድረግ ይቻላል:: በዚህ ሂደት የሰዎቹን ክፉ ሥራ በመልካም ሥራ አሸነፍን ማለት ነው:: ነገር ግን እነርሱ ክፉ ሲያደርጉ ክፉ ብድራት ከመለስን እኛም እንደ እነርሱ ሆን ማለት ነው:: በክፉ ፈንታ ክፉ መመለስ ከትልቅ የሥነምግባር ደረጃ ራሳችንን በራሳችን ድርጊት ማዋረድ-ነው::



ጠላትን ወዳጅ ማድረግ ግን ማንም ሰው የሚያደርገው ነገር እንደሆነ አይታሰብም:: ይህን ለማከናወን ጠላትነትን አጥፍቶ ወዳጅነትን ማምጣት የሚቻልበትን ስልቶች ማወቅና ተግባራዊ ማድረግን ይጠይቃል:: ከሁሉም በላይ ወዳጅነት የሚመጣው ለጠላት መልካም ነገር በማድረግ ነው:: ለጠላቶቻቸው መልካም በማድረግ ጠላቶቻቸውን ያጠፉ ምሳሌ የሚሆኑልን ሰዎች አሉ:: ከእነዚህም የሚከተሉትን ሰዎች እንመለከታለን:: እነርሱም:-

ኤልሳዕ:- በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ካስነሳቸው ነቢያት መካከል አንዱ ኤልሳዕ ነበር:: ኤልሳዕ በሚያገለግልበት ወቅት የሶርያ አደጋ ጣዮች እርሱ ወደ ነበረበት ሥፍራ መጡ:: እነዚህ ወታደሮች በሶርያ ንጉሥ ተልከው የመጡ ሲሆን ዓላማቸውም ለእስራኤል ንጉሥ ምስጢር እየነገረው የሚያስመልጠውን ነቢዩ ኤልሳዕን ለመያዝ ወይም ለማጥቃት ነበር:: ኤልሳዕም እግዚአብሔር ዓይናቸውን እንዲያሳውር ለመነ:: የአደጋ ጣዮችም ዓይን ታወረ:: ከዚያም በጠላት የሚፈልገው እርሱ ራሱ ወታደሮቹን መርቶአቸው የእስራኤል ንጉሥ ወደሚገኝበት ወደ ሰማርያ ወሰዳቸው:: ከዚያም እንደ ደረሰ እግዚአብሔር ዓይናቸውን እንዲከፍት ጠየቀ! ሆነለትም:: ጠላቶቹ በእርሱ እጅ እንደገቡ የተመለከተው የእስራኤል ንጉሥ «ልግደላቸውን?» ብሎ ኤልሳዕን ጠየቀ:: ይህ ንጉሥ አንድ የሚያውቀው ሐቅ ነበር:: በማንኛውም መንገድ ጠላት በእጅ ውስጥ ከገባ ማጥቃትን ነው:: ጠላትን አግኝቶ ምሕረት የሚያደርግ ሰብዓዊ ፍጡር እምብዛም አይገኝም::

ከዚህ ከሰብዓዊ ፍጡር እይታና ድርጊት የተለየ አመለካከት የነበረው ነቢዩ ኤልሳዕ ግን ያልተለመደ ነገርን አደረገ:: በኤልሳዕ ትዕዛዝ መሠረት ለአደጋ ጣዮቹ ድግሥ ተዘጋጀላቸው:: «ብዙም መብል አዘጋጀላቸው! በሉና በጠጡ ጊዜም አሰናበታቸው! እነርሱም ወደ ጌታቸው ሄዱ» (2ነገ6:23ሀ)::

የኤልሳዕ ውሳኔ አጉል ሃይማኖተኛነት ሊመስል ይችላል:: በሕዝቡ ላይ በማንኛውም ጊዜ አደጋ መጣል የሚችሉትን ሰዎች ይዞ ድግሥ አብልቶ ማሰናበት የሞኝነት ድርጊት ይመስላል:: ኤልሳዕ ግን የተረዳው እውነት ነበር::

- በሕያው እግዚአብሔር ጥበቃ መታመን ለሕዝቡ ደህንነት ዋስትና ነው:: እነዚህን ጠላቶች አሳልፎ የሰጣቸው እግዚአብሔር ነው እንጂ የሕዝቡ የውትድርና ብቃት እንዲሁም የራሱም ችሎታ እንዳልሆነ ተረድቷል::
- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ከሆነ ምንም ያህል ጠላት ቢመጣ ወይም ብዙ ተቃዋሚ ቢኖር ዞሮ ዞሮ ድሉ የእግዚአብሔር መሆኑን ተገንዝቧል::
- እንደ እግዚአብሔር ነቢይነቱ የጠየቀውን ነገር እግዚአብሔር እንደሚፈጽምለት ቢያውቅም እግዚአብሔር እርሱን ለማጥፋት የመጡትን ወታደሮች እንዲያጠፋ አልለመነም:: ምሕረት ከፍርድ እንደሚበልጥ የተገነዘበ ሰው ነበር::

- ጠላትን መበቀል ከሚያመጣው ፍሬ ይልቅ ለጠላት መልካም ማድረግ ዘላቂነት ያለው ሰላምን እንደሚያመጣ ገብቶታል:: መጽሐፉ «ከዚያም በኋላ የሶርያ አደጋ ጣዮች ወደ እስራኤል አገር አልመጡም» (2ነገ6:23ለ) ይላል:: ለኤልሳዕ በጠላት ላይ እጅግ የከበረ ድል መቀዳጀት የሚባለው ጠላትነትን ወደ ወዳጅነት መለወጥ እንደሆነ ተረድቷል::

ኤልሳዕ በዚህ መልካም ድርጊቱ ጠላት በእኛ ላይ ክፉ ሲያስብና ሲያደርግ በመልካም መንገድ እምንታዊ ምላሽ መስጠት እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝበት እንደሆነ ያስተምረናል:: ለጠላት ለናይ የሆነ ተግባር መፈጸም በሰብዓዊ እይታ የተለመደ ባይሆንም መንፈሳውያን የሆኑ ሰዎች ግን ይህ አካሄድ በግል ሰብዓዊ የሆነ እርምጃ ከመውሰድ የላቀ ውጤት እንደሚያስገኝ ያምናሉ::

ዳዊት:- መጽሐፍ ቅዱስ የገዛ ጠላቶቻቸው በእጃቸው ውስጥ ገብተው እያሉ ምሕረት ስላደረጉት ሰዎች ይናገራል:: ከእነዚህም አንዱ ዳዊት ነው:: ሳኦል የተባለ የእስራኤል ንጉሥ እግዚአብሔርን ባለመታዘዙ ምክንያት በእርሱ ከተናቀ በኋላ ዳዊትን ለንጉሥነት መረጠ:: ዳዊት ምንም ለንጉሥነት የተቀባ ሰው ቢሆንም ሳኦልን በታማኝነት ያገለግለው ነበር:: በእግዚአብሔር እርዳት ጎልያድ የተባለውን የፍልስጥኤማውያንን ጀግና ካሸነፈ በኋላ የእስራኤል ሴቶች ሳኦል ሺህ፣ ዳዊት ደግሞ እልፍ ገደለ ብለው ከመዘመራቸው የተነሣ ሳኦል ለእርሱ የተሰጠው ክብር አነስተኛ እንደሆነ በማሰብ ዳዊትን ለመግደል አሰበ:: በተለያዩ መንገዶች ለእርሱ ወጥመድ በማዘጋጀት ዳዊትን ለመግደል ያደረገው ሙከራ አልተሳካለትም:: በመጨረሻ ጦር በማስከተት ዳዊት ላይ ዘመቻ ከፈተ::

ሳኦል ዳዊትን በማሳደድ ላይ በነበረበት ሁኔታ በአንድ አጋጣሚ ሳኦል ዳዊትና ወታደሮቹ በነበሩበት ዋሻ ውስጥ ሲፀዳዳ ይገባል:: በዚህ ጊዜ «የዳዊትም ሰዎች - እነሆ ጠላትህን በእጅህ አሳልፌ እሰጠዋለሁ፣ በዓይንህም ደስ የሚያሰኝህን ታደርግበታለህ ብሎ እግዚአብሔር የነገረህ ቀን እነሆ ዛሬ ነው» (1ሳሙ24:4) በማለት ዳዊት ጠላቱን ሳኦልን እንዲገድለው ይመክሩታል:: በሰብዓዊነት እይታ ሲታይ የዳዊት ወዳጆች የተናገሩት ነገር ትክክለኛ አሳብ ይመስላል:: የሚገርመው ነገር እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔር ስለዳዊት የተናገረውንም የተስፋ ቃል ጠቅሰዋል:: እግዚአብሔር በእርሱ ላይ የሚነሡትን ጠላቶቹን በእጁ አሳልፎ እንደሚሰጥና ድልን እንደሚያቀዳጀው የስጠው የተስፋ ቃል ፍጻሜው አሁን እንደሆነ አሳለቡት:: የትንቢቱ መኖርና የሳኦል በዳዊት እጅ መውደቅ መገጣጠም ሁኔታው ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቆረጠ እንደሆነ ለመገመት ያስችላል:: በጠላት ላይ የማያዳግም እርምጃ በመውሰድ ከስደት ኑሮ ለመውጣትና የንጉሥነት ዙፋንን ለመቆጣጠር ሁኔታው ምቹ ሆኖ ቀርቧል::

የዳዊት እይታ ግን የተለየ ነበር:: ዳዊት ይህን አጋጣሚ በመጠቀም የመከራውን ጊዜ ለማሳጠር አልፈለገም:: የሚያሳድደውን ጠላቱን ሳኦልን ገድሎ ሥልጣን መያዝ ቀርቶ በቀስታ የሳኦልን መጎናጸፊያ ዘርፍ



በመቁረጡም ልቡ በሐዘን ተመታ:: ዳዊት ጠላቱን ለመግደል ያልፈለገበት ምክንያት ምን ነበር?

- ✓ ዳዊት እግዚአብሔር የቀባውን ሰው መግደል አልፈለገም:: «እግዚአብሔር የቀባው ነውና እግዚአብሔር በቀባው ላይ እንዲህ ያለውን ነገር አደርግ ዘንድ እጄንም አጥልበት ዘንድ እግዚአብሔር ከእኔ ያርቀው» (1ሳሙ24:6) በማለት ተናገረ::
- ✓ ዳዊት ሳኦልን ለመግደል ምንም ዓላማ እንደ ሌለው በማስረጃ ለማረጋገጥ ፈልጎ ነበር:: ዳዊት ከሳኦል ጋር በተገናኘ ጊዜ «የልብስህን ዘርፍ በቆረጥሁ ጊዜ አልገደልሁህም ስለዚህም በእጄ ክፋትና በደል እንደሌለ አንተም ነፍሴን ልትወስድ ምንም ብታሳድደኝ እንዳልበደልሁህ ተመልከተህ እወቅ» (1ሳሙ24:11) በማለት ተናገረው::
- ✓ ዳዊት ይህን መልካም ድርጊት በማድረጉ ምናልባት ሳኦል ተጸጽቶ እርሱን ከማሳደድና በጠላትነት ከመፈለግ ይመለስ ይሆናል ብሎ ተስፋ በማድረግ ነበር::

ዳዊት ባላለበው ሁኔታ ሳኦልን ለመግደል በሚችልበት ሥፍራ ማግኘቱ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላከለት ፈተና እንደሆነም ማሰብ ይቻላል:: ተሳዳጅ በርቀት በሚኖርበት ጊዜ አሳዳጅን እንደማይጠላና ቢያገኘውም ምሕረት እንደሚያደርግለት መናገር ይችላል:: ይህ አባባል ግን እርግጠኛነቱ ማለት ከልብ የተነገረ መሆኑ የሚታወቀው በተግባር አሳዳጅ በተሳዳጅ እጅ ወድቆ ቢታይ ነው:: ዳዊት በልቡ ውስጥ በተጠራቀመው ጥላቻና ምሬት ተሞልቶ ሳኦልን ይገድላል ወይስ በይቅርታ ተሞልቶ ምሕረት ያደርግለታል? ለሚለው ጥያቄ ትክክለኛ ምላሽ የሚገኘው ሳኦልን በዳዊት እጅ ጥሎ ማየት ነበር::

በሰብዓዊ እይታ በሚገርም መልኩ ሳኦል ዳዊትን ለመግደል ብዙ ሙከራ ቢያደርግም አሁንም እያሳደደው እያለ ዳዊት በእርሱ ላይ ቂም አልያዘም:: በእርሱ ልብ ጥላቻ፣ ቂምና በቀል ሥፍራ አላገኙም ነበር:: ባገኘው አጋጣሚ ሳኦልን መግደል ቀርቶ የእርሱን ልብስ ጫፍ መቁረጡም ራሱ የሐዘን ምክንያት ቢሆንበት እንመለከታለን:: «የሳኦልን የልብሱን ዘርፍ ስለ ቆረጠ የዳዊት ልብ በኀዘን ተመታ» (1ሳሙ24:5):: ይህ ዳዊት ምን ያህል ለእግዚአብሔር ፈቃድና ሕግ የተነቃቃ ልብ ወይም መንፈሳዊነት ሚዛን ሊለቅ የሚለማው እንደሆነ መመልከት ይቻላል:: የሳኦልን የልብሱን ዘርፍ መቁረጥ ለሳኦል ውርደትን ያመጣል:: ዳዊት እግዚአብሔር በሥልጣኑ ባነገሠው ሰው ላይ ውርደትን ማምጣት ትክክል እንዳልሆነ በደንብ የገባው ሰው ነበር::

ዳዊት ለሳኦል መልካም ነገር በማድረጉም የተገኘው ውጤት ጥሩ ነበር:: ዳዊት በክፉ ፈንታ መልካም እንደ መለሰለት፣ ከሳኦል ይልቅ ዳዊት ጻድቅ እንደሆነ፣ በሰብዓዊ እይታ ማንም ሰው ጠላቱን በእጅ አግኝቶ እንደማይተው ነገር ግን ዳዊት ምሕረት እንዳደረገለት ሳኦል ተገነዘበ:: ከእርሱም ይልቅ ዳዊት ለንጉሥነት ብቃት ያለው ሰው እንደሆነ አስመሰከረ:: በእርሱ ላይ

